# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ

# ሪፑብሊክ መንግስት



## በምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደር እና ቁጥጥር ባለስልጣን መ/ቤት

## በግል የጤና ተቋማት የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ

## ላይ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት

## ሪፖርት

ሐምሌ 2005 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# ማውጫ


**ክፍል አንድ** ........................................................................................ 1

*መግቢያ*........................................................................................1

የባለስልጣን መ/ቤቱ ተልዕኮና ራዕይ ..................................................2

የባለስልጣኑ መ/ቤት ስልጣንና ተግባር..................................................3

ድርጅታዊ መዋቅር........................................................................5

የሰው ኃይል .................................................................................5

የፋይናንስ ምንጭ..........................................................................6

የኦዲቱ አላማ.................................................................................6

የኦዲቱ አካባቢ ...............................................................................6

የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች ...........................................................6

የኦዲት መመዘኛ መስፈርት ................................................................7

የኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ .................................................................... 7

የግል የጤና ተቋማት የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ የሥራ ሂደት ፍሰት ........................7

**ክፍል ሁለት** ........................................................................................ 9

የኦዲት ግኝቶች................................................................................9

**ክፍል ሶስት** ........................................................................................26

*መደምደሚያዎች* ............................................................................26

**ክፍል አራት** ........................................................................................28

*የማሻሻያ ሃሳብ*..............................................................................28

**አባሪ 1 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች**..................................................30

**አባሪ 2 በናሙና ተመርጠው የታዩ የግል የጤና ተቋማት** ..................................33

# ክፍል አንድ

***መግቢያ***

1. *ሀገራችን ኢትዮጵያ በሁሉም የስራ መስክ ብቁ የሆነና ምርታማ ዜጋን ለማፍራት የህብረተሰቡንም ሆነ የእንስሳቱን ጤና የተሟላ ማድረግ ይኖርበታል፡፡ የጤና አገልግሎት ዕድገት ለኢኮኖሚና ማህበራዊ ልማት አስፈላጊ ከሆኑ ጥልቅ ግብዓቶች አንዱ ነው፡፡*
2. *የጤና ችግር በመሠረታዊ የጤና ክብካቤ የሕዝቡን ስነልቦናዊ አመለካከት በመለወጥ ሊፈታ እንደሚችል በመታመኑ ህብረተሰቡ በየደረጃው ጤናውን እንዲጠብቅና የወደፊቱም ትውልድ ጤናው ተጠብቆ ኃላፊነቱን እንዲረከብ ለማስቻል የጤና አጠባበቅ ህግ በማስፈለጉ በአዋጅ ቁጥር* 200/1992 *የህዝብ ጤና አጠባበቅ በአገሪቷ የጤና ፖሊሲ የአካባቢ ደህንነት መጠበቅ እንዳለበት፣ ከሆስፒታል የሚወጡ ደረቅ፣ፍሳሽ ወይም ሌሎች ቆሻሻዎች በከፍተኛ ጥንቃቄ መያዝ እንዳለባቸው ተገልጿል፡፡*
3. *የአካባቢ ጤና አገልግሎት ሥራን ተፈጻሚ ለማድረግ ኃላፊነቱ በመጀመሪያ በጤና ጥበቃ ሚኒስትር የሃይጂንና አካባቢ ጤና አገልግሎት መምሪያ ሲሆን አሁን ግን በአዋጅ ቁጥር* 661/2002 *ለተቋቋመው ለኢትዮጵያ የምግብ ፣መድሃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደር እና ቁጥጥር ባለስልጣን ተሰጥቷል፡፡*

***<u>ከጤና ተቋማት የሚወጡ ቆሻሻዎች የሚያስከትሉት ችግር</u>***

4. *በየትኛውም የዓለም አገራት* (*ባደጉትም ሆነ በማደግ ላይ ባሉት*) *የቆሻሻ አስተዳደር ሥራ የሰውና የእንስሳትን ጤና ለመጠበቅና የአካባቢ ጥበቃን ዕውን ለማድረግ ዋነኛ ጉዳይ ሆኖ ይገኛል፡፡ የጤና ተቋማት ማለት የምርመራና ሕክምና፣ የጤና ምርመራ፣ የማይክሮ ባዮሎጂካል፣ የኬሚካል፣ የቶክሲኮሎጂካል ምርመራ ሥራ የሚካሄዱባቸውን ድርጅቶችን ያጠቃልላል፡፡ የጤና ተቋማት ቆሻሻ የሚፈረጀው አደገኛነት ባላቸው ቆሻሻዎች* (hazardous waste) *ውስጥ ሲሆን፣ ይህም ከሰውና ከእንስሳት በሽታ ጋር የተጣመረ ነው፡፡ ይህ ዓይነቱ ቆሻሻ የሚያካትታቸው መድኃኒቶች፣ ሹልና ስለት ያላቸው ነገሮች*(*መርፌ፣ ሲሪንጅ፣ ምላጭ* … )*፣ ቁስል የታሸገባቸው ፋሻዎች፣ ከሰውነት የሚወጡ ፈሳሾችና የሰውነት አካላት* (*ደም፣ የደም ተዋጽኦ፣ ተቆርጦ የሚቀር የሰውነት ክፍል፣ ብልቶች*) *ሲሆኑ እነዚህም የቫይረስ፣ የባክቴሪያና ጥገኛ የሆኑትን የበሽታ ዘሮችን የሚይዙ በመሆኑ በትክክሉና በጥንቃቄ ካልተያዙና ካልተወገዱ አደገኛ በሽታዎችን ሊያሰራጩ የሚችሉ ናቸው፡፡*

5. በአግባቡ ያልተጠበቀና በትክክለኛው መንገድ እንዲወገድ ያልተደረገ የሜዲካል ቆሻሻ አካባቢን /ውሃ፣ አፈርና አየር/ በመበከል በሰው፣ በእንስሳትና ሕይወት ባላቸው ነገሮች ዕፅዋትን ጨምሮ በሽታን በማስከተል ለሞትና ጥፋት ይዳርጋል፡፡ ከዚህ አደገኛነት ይዘትና ጠባይ በመነሳትም የሜዲካል ቆሻሻ ከሌሎች የከተማ ቆሻሻዎች ጋር ሳይገናኝ በዚያው በአመንጪው አካል በአግባቡ መጠበቅና በትክክለኛው መንገድ መወገድ ይኖርባቸዋል፡፡
6. በሕይወትና በጤና ላይ ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት ለመከላከል እንዲያስችልም በሜዲካል ቆሻሻ ሳቢያ ሊደርሱ የሚችሉትን ጉዳቶች፣ የቆሻሻዎቹን ዓይነትና የጠንቀኝነት ደረጃ፣ እንዲሁም መሰረታዊ የመከላከያ ዘዴዎችን ለይቶ ማወቅ፣ ከአጠባበቁ እስከ አወጋገዱ ሊኖር ስለሚገባው ጤናማ አሰራር አግባብነት ያለው የአሠራርና የቁጥጥር ሥርዓት መዘርጋትና ተግባራዊ ማድረግ የግድ ይሆናል፡፡
7. በተለያዩ አካላት ሲሠሩ የቆዩትን የጤና የቁጥጥር ተግባራት ወደ አንድ በማሰባሰብ ቁጥጥሩ ወጥነት ያለው ስርዓት እንዲኖረው በማድረግ አፈጻጸሙን ወደ ተሻለ ደረጃ ለማሸጋገር የጤና ሴክተሩን ራዕይና ተልዕኮ ማሳካት የሚችል አዲስ የአደረጃጀት ሥርዓት ለመፍጠር በ2002 ዓ.ም በአዋጅ ቁጥር 661/2002 የኢትዮጵያ የመድኃኒት አስተዳደር እና ቁጥጥር ባለስልጣን የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደር እና ቁጥጥር ባለስልጣን እንዲቋቋም ተደርጓል፡፡

---

<u>**የባለስልጣን መ/ቤቱ ተልዕኮና ራዕይ**</u>

**ተልዕኮ**

8. የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ተቋማት እንዲሁም የጤና ባለሙያዎችን የብቃት ማረጋገጫ በመስጠትና በመቆጣጠር፣ በምዝገባና በጥራት ምርመራ የግብዓቶች ጥራት፣ ደህንነትና ፈዋሽነት በማረጋገጥ እንዲሁም አግባባዊ አጠቃቀምን ለማስፈን ወቅታዊ መረጃዎችን በማቅረብ የህብረተሰቡን ጤና ማበልጸግና መጠበቅ ነው፡፡

**ራዕይ**

9. ጥራት ያለው የጤና አገልግሎትና ግብዓት ለሁሉም ዜጎች

## የባለስልጣኑ መ/ቤት ስልጣንና ተግባር

10. የምግቦችን ደህንነትና ጥራት፣ የመድኃኒቶችን ደኅንነት፣ ፈዋሽነት፣ ጥራትና አግባባዊ አጠቃቀም የሕክምና ባለሙያዎችን ብቃትና አሠራር፣ የሀይጅንና የአካባቢ ጤናን እና የጤናና ጤና ነክ ቁጥጥር የሚደረግበት ተቋማትን የቁጥጥር ደረጃዎች አዘጋጅቶ አግባብ ላለው አካል ያቀርባል፣ ሲጸድቁም በተግባር ላይ መዋላቸውንና መከበራቸውን ያረጋግጣል፤

- ለልዩ የጤና ተቋማት፣ ለምግብ ወይም ለመድኃኒት አምራች ድርጅቶች፣ ለጥራት መቆጣጠሪያ ላቦራቶሪዎች፣ ለባዮኢኩቫለንስ ማእከላት፣ ለአስመጪዎች፣ ለላኪዎች፣ ለአከማችና ለአከፋፋይ ድርጅቶች እና ለክልል ተሻጋሪ የጤና አገልግሎት ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ያግዳል፣ ይሰርዛል፤
- የምግብ፣ የመድኃኒት፣ የጤና ባለሙያዎችና የጤና ተቋማት ጥራትና ብቃት የሚጠናከርበትንና የሚስፋፋበትን ፖሊሲ ሀሳብ ያመነጫል፣ ረቂቅ ሕጎችን ያዘጋጃል፣ ለመንግሥት ውሳኔም ያቀርባል፤
- የምግብ፣ የመድኃኒት፣ የአካባቢ ጤና አጠባበቅ፣ የጤና ባለሙያዎች እና የጤናና ጤና ነክ ቁጥጥር የሚደረግበት ተቋማትን በሚመለከት የመረጃዎች ማዕከል ሆኖ ያገለግላል፤
- በምግብ ወይም በመድኃኒት መመረዝ ወይም መበከል ምክንያት ለሚደርስ የሞት፣ የጤንነት መታወክ መንስኤ የሆነውን ንጥረ ነገር ልዩ ልዩ ናሙናዎችን በመውሰድ ወይም በመቀበል መርምሮ ምንነታቸውን ያረጋግጣል፣ አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል፤
- ለሥራው አስፈላጊ የሆኑትን የጥራት ምርመራ ላቦራቶሪዎችን ያደረጃል፤
- ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ወይም ወደ ውጭ ሀገር የሚላኩ ምግቦች፣ መድኃኒቶች፣ ጥሬ ዕቃዎች፣ የማሸጊያ ቁሳቁሶችና የአስክሬን ቁጥጥር ያካሂዳል፣ የመግቢያና የሙውጫ ፍቃዶች ይሰጣል፤
- የሀገሪቱን የመድኃኒት መዘርዝር ያዘጋጃል፣ በመዘርዝሩ የተካተቱትን መድኃኒቶች፣ በደረጃ ይመድባል፣ መዘርዝሩን እንደአስፈላጊነቱ ይከልሳል፤
- የምዝገባ መስፈርቶችን መሠረት በማድረግ መድኃኒቶችን ይገመግማል፣ ይመዘግባል፣ ምዝገባውን ያድሳል፣ ያግዳል፣ ይሰርዛል፤

- የምግቦችን ደህንነት፣ ጥራት እና የመድኃኒቶችን ደህንነታቸው፣ ፈዋሽነታቸውና ጥራታቸውን ገበያ ላይ ከዋሉ በኋላ ለማረጋገጥ የድህረ ገበያ ቅኝት በማካሄድ ተገቢውን የቁጥጥር ሥራ ያካሂዳል አስፈላጊውን እርምጃም ይወስዳል፤
- የሕክምና ሙከራ ጥያቄዎችን እየመረመረ ይፈቅዳል፣ ሂደቱ በመልካም የሕክምና ስርዓት መሠረት መፈፀሙን ይከታተላል፣ ውጤቱንም ይገመግማል፣ ለሀገሪቱ በሚጠቅም ሁኔታ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ይፈቅዳል፣ አስፈላጊ ሲሆንም የሕክምና ሙከራውን ያግዳል ወይም ያስቆማል፤
- የናርኮቲክ መድኃኒቶች፣ ሳይኮትሮፒክ ንጥረ ነገሮች እና ፕሪከርሰር ኬሚካሎች ማምረትን፣ ማስመጣትን፣ መላክን፣ ማከፋፈልን፣ ለህሙማን ማዘዝን፣ ማደልን፣ አጠቃቀምን፣ መመዝገብንና ሪፖርት ማድረግን ይቆጣጠራል፣ አለአግባብ መጠቀምን ይከላከላል፣ ለዓለም አቀፍ ናርኮቲክ ቁጥጥር ቦርድ ሪፖርት ያቀርባል፤
- ትምባሆ ማስመጣትን፣ ስርጭትን፣ ሽያጭን፣ አጠቃቀምን፣ አስተሻሸግና መለያ አሰጣጥን፣ ማስተዋወቅንና አወጋገድን ይቆጣጠራል፤
- ወደ አገር በሚገቡ አውሮፕላኖች ላይ ከጤና አጠባበቅና ተላላፊ በሽታዎች ቁጥጥር ጋር ተያያዥነት ያለው ኢንስፔክሽን ያካሂዳል፣ እንዲሁም ከአገር በሚወጡ አውሮፕላኖች ላይ ርጭት ያካሂዳል ሰርተፊኬትም ይሰጣል፤
- በመግቢያና መውጫ ኬላዎች ላይ ወደ አገር ውስጥ በሚገቡ ወይም በሚወጡ አለም አቀፍ መንገደኞች ላይ ተላላፊ በሽታዎችን በተመለከተ ቁጥጥር ያካሂዳል፣ እንደ አስፈላጊነቱም ወደ አገር ውስጥ እንዳይገቡ፣ ከአገር እንዳይወጡ ወይም እንዲገለሉ ያደርጋል፤ ከአንድ ክልል በላይ የሆነ የወረርሽኝ በሽታ ሲከሰት አስፈላጊ የመከላከልና የመቆጣጠር ሥራ መካሄዱን ያረጋግጣል፤
- በበቂ መጠን የማይገኙ የጤና ባለሙያዎች፣ ለአማራጭና ተደጋጋፊ ህክምና ባለሙያዎች እና በግልም ሆነ በቡድን ከውጭ የህክምና አገልግሎት ለመስጠት ለሚመጡ የጤና ባለሙያዎች የሙያ ፈቃድ ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ያግዳል፣ ይሰርዛል፤
- የአገልግሎት ጊዜያቸው ያበቃ ምግቦች፣ መድኃኒቶችና ጥሬ ዕቃዎቻቸው በአግባቡ መወገዳቸውን ያረጋግጣል፤
- ከተለያዩ ተቋማት የሚወጡ ክልል ተሻጋሪ የደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ በሕዝብ ጤና ላይ ጉዳት የማያስከትል መሆኑን ያረጋግጣል፣ ይቆጣጠራል፤

- ሕገወጥ ምግቦችን፣ መድኃኒቶችና የጤና አገልግሎቶችን ይቆጣጠራል፣ አስፈላጊ እርምጃዎችንም ይወስዳል፤
- ከአንድ ክልል በላይ ለህብረተሰቡ ለመጠጥ የሚቀርብ ውኃ የጥራት ደረጃውን የጠበቀ መሆኑን ያረጋግጣል፤
- በፌዴራል መንግሥት ስር ያሉ ጤና ነክ ቁጥጥር የሚደረግበት ተቋማት ተገቢውን የሐይጅንና አካባቢ ጤና አገልግሎት መስፈርት ማሟላታቸውን ያረጋግጣል፤
- በፌዴራልና በክልል ያለው የቁጥጥር ሥራ ተመጋጋቢና ተደጋጋፊ እንዲሆን ለማድረግ ለክልል የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ስራ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፡፡

## ድርጅታዊ መዋቅር

11. ባለስልጣን መ/ቤቱ በአንድ ዋና ዳይሬክተር፣ በሁለት ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች /የደረጃና ፈቃድ ምክትል ዋና ዳይሬክተር እና የኢንስፔክሽንና የህግ አፈፃፀም ምክትል ዋና ዳይሬክተር/ የሚመራ ሲሆን ለዋና ዳይሬክተሩ ተጠሪ የሆኑ 3ት ዳይሬክቶሬቶች አሉት እነሱም የሰው ሀብት ሥራ አመራር ዳይሬክቶሬት፣ የፋይናንስ አቅርቦት ዳይሬክቶሬት እና የንብረት ጠቅላላ አገልግሎት ዳይሬክቶሬቶች ናቸው፡፡ ባለሥልጣን መ/ቤቱም ተጠሪነቱ ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ነው፡፡
12. ባለስልጣኑ እና የክልል ጤና ቢሮዎችም በሥራቸው እና በአካባቢዎቻቸው ለሚገኙ የመንግስትና የግል ጤና አገልግሎት ተቋማት ፈቃድ የመስጠት ፣መመሪያ የማዘጋጀት፣ ተፈጻሚነታቸውንም የመከታተል ኃላፊነት ተሰጥቷቸዋል፡፡

## የሰው ኃይል

13. በባለስልጣን መ/ቤቱ በመዋቅሩ መሰረት ከሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር 581 የሥራ መደቦች የተፈቀዱለት ሲሆን በህዳር ወር 2005 ዓ.ም ያለው የሰው ኃይል ብዛት 432 ሲሆን ከዚህ ውስጥ 247ቱ ወንዶች እና 185ቱ ሴቶች ናቸው፡፡ 149 የሥራ መደቦች ግን በክፍትነት የሚገኙ ናቸው ፡፡
14. ከግል የጤና ተቋማት/ቲቺንግና ስፔሻላይዝድ ሆስፒታሎች/ የሚወጡ ቆሻሻዎች አያያዝና አወጋገድን የሚከታተለው የኢንስፔክሽን ቅኝት ዳይሬክቶሬት ሲሆን በስሩ 15 ሰራተኞች ይገኛሉ፡፡

## የፋይናንስ ምንጭ

15. ባለስልጣን መ/ቤቱ ከመንግስት ከሚመደብለት ዓመታዊ በጀት፣ ለሚሰጠው አገልግሎት ከሚያስከፍለው ክፍያና ከሌሎች ምን□ ች ገቢ የሚያገኝ ሲሆን፣

- በ2002 ዓ.ም ለመደበኛና ለካፒታል በጀት ብር 14,057,125.00 የተመደበለት ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር 11,160,093(79%) ወጪ ሆኗል፣
- በ2003 ዓ.ም ለመደበኛና ለካፒታል በጀት ብር 32,221,827.72 የተመደበለት ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር 28,307,612(87%) ወጪ ሆኗል፣
- በ2004 ዓ.ም ለመደበኛ እና ለካፒታል በጀት ብር 32,970,428.30 የተመደበለት ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር 31,353,753(95%) ወጪ ሆኗል፣

## የኦዲቱ አላማ

16. የኦዲቱ ዓላማ ከግል የጤና ተቋማት የሚወጡ ቆሻሻዎች አያያዝ፣ አወጋገድ፣ ክትትል እና ቁጥጥር የህብረተሰቡን ጤና ለመጠበቅና የአካባቢ ደህንነትን ለማረጋገጥ በሚያስችል መልኩ እየተከናወነ መሆኑን ለማረጋገጥና ይህንን በተመለከተ የአሰራር ችግሮች ካሉ ችግሮቹን ለይቶ በማውጣት ችግሮቹን ለማስወገድ ወይም ለመቀነስ የሚያስችሉ የማሻሻያ ሀሳቦችን (Recommendations) ለማቅረብ እና ተጠያቂነትን ለማጠናከር ነው፡፡

## የኦዲቱ አካባቢ

17. ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ የግል ጤና ተቋማት የህክምና ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ የአካባቢውን እና የሕብረተሰቡን ጤና በማይበክል እና በማይጎዳ መልኩ እየተከናወነ መሆኑን ማረጋገጥ ነው፡፡

## የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች

18. የግል የጤና ተቋማት የቆሻሻ አያያዝ፣ አወጋገድ፣ ክትትልና ቁጥጥር ላይ ሊከናወን ለታቀደው የክዋኔ ኦዲት ሁለት የኦዲት ጭብጦች(Issues) ተለይተዋል እነሱም፡-

- ከግል ጤና ተቋማት የሚወጡ ቆሻሻዎች አያያዝና አወጋገድን በተመለከተ መመሪያዎች መኖራቸውንና በጤናው ዘርፍ ለተሰማሩ ሠራተኞች ስልጠና መሰጠቱን እና ከባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ መተግበራቸውን ማጣራት፣

- ከግል የጤና ተቋማት የሚወጡ ቆሻሻዎች አሰባሰብ፣ አያያዝ፣ አጓጓዝና አወጋገድ ስርዓት ባለው ሂደት፣ ባለስልጣን መ/ቤቱ ባወጣቸው መመሪያና ስታንዳርድ መሠረት የሚከናወኑ መሆኑ እና በዚሁ መሠረት ክትትል እና ቁጥጥር የሚደረግ መሆኑን ማጣራት፣

የሚሉ ናቸው፡፡

## የኦዲት መመዘኛ መስፈርት

19. ከላይ ለተመረጡት ሁለት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች ለመመዘን የሚያስችሉ 26 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative Criteria) ተዘጋጅተዋል፡፡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶችን ለማዘጋጀት ለቆሻሻ አያያዝና አወጋገድን በተመለከተ Health care waste management directorate በሚል የተዘጋጀው መመሪያ፣ ሆስፒታሎች ሲከፈቱ ማሟላት ስለሚገባቸው ነገሮች የሚገልፀው ስታንዳርድ (National minimum standard for health center) እና የባለስልጣን መስሪያ ቤቱ አዋጅ መሰረት ሆነዋል፡፡ የመመዘኛ መስፈርቶቹም ከዚህ ሪፖርት ጋር **በአባሪ 1** ተያይዟል፡፡

## የኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ

20. ኦዲቱ የሚሸፍነው ከ2002 - 2004 በጀት ዓመት ድረስ በግል የጤና ተቋማት የሚወጡ ቆሻሻዎች አያያዝና አወጋገድን በተመለከተ የተከናወኑ ሥራዎችን ነው፡፡ ኦዲቱ በዋነኛነት የተከናወነው በባለስልጣን መ/ቤቱ ፣ ባለስልጣን መ/ቤቱ ፍቃድ በሰጣቸው የግል የጤና ተቋማት፣ በናሙና በተመረጡ በአዲስ አበባ ጤና ቢሮ ስር በሚገኙ 10 ሆስፒታሎችና 8 ከፍተኛ ክሊኒኮች፣ በደቡብ ጤና ቢሮ ስር በሚገኙ 4 ሆስፒታሎችና 10 ከፍተኛና መካከለኛ ክሊኒኮች እና በኦሮሚያ ጤና ቢሮ ስር በሚገኙ 4 ሆስፒታሎችና 10 ከፍተኛና መካከለኛ ክሊኒኮች መረጃዎችን በመከለስ፣ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎቹም ቃለ መጠይቅ በማቅረብ እና አሠራሩን በአካል በመመልከት ነው፡፡

## የግል የጤና ተቋማት የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ የሥራ ሂደት ፍሰት

21. በባለስልጣን መ/ቤቱ የግል የጤና ተቋማት የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ በኢንስፔክሽንና ቅኝት ዳይሬክቶሬት ስር ባለ የኢንስፔክሽን ቅኝት ቡድን ክትትልና ቁጥጥር የሚያደርግ

ቢሆንም በግልፅ የተቀመጠ የሥራ ፍሰት ሂደቱን የሚያሳይ መረጃ አላገኘንም፡፡ ከዚህ በፊት በጤና ተቋሞች ተፈፃሚ የሚሆን የቆሻሻ አያያዝ አወጋገድ መመሪያ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የተዘጋጀና ስራ ላይ የዋለ ቢኖርም በአሁኑ ሰዓት በባለስልጣን መ/ቤቱ አዲስ መመሪያ ረቂቅ በማዘጋጀት ላይ ነው፡፡

# ክፍል ሁለት

# የኦዲት ግኝቶች

**ከግል የጤና ተቋማት የሚወጡ ቆሻሻዎችን ለመከታተል በዕቅድ መያዙን በተመለከተ**

22. ከጤና ተቋማት የሚወጡ ቆሻሻዎች አያያዝና አወጋገድን የሚከታተል አካል/ክፍል/ ለሚያከናውነው ተግባራት የረጅምና የአጭር ጊዜ ዕቅድ ሊያዘጋጅና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ ነገር ግን ከግል የጤና ተቋማት የሚወጡ ቆሻሻዎች በሰውና በእንስሳት ላይ የሚያስከትሉት ጉዳት ከፍተኛ ቢሆንም ባለስልጣን መ/ቤቱ ቁጥጥርና ክትትል ለማድረግ በዕቅድ ያልያዘ መሆኑ ታውቋል፡፡
23. የግል የጤና ተቋማትን የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድን ለመቆጣጠር ባለስልጣን መ/ቤቱ በ2003 ዓ.ም እና በ2004 ዓ.ም ዕቅድ ያልያዘ መሆኑ፣ የክልል ጤና ቢሮዎችም /አዲስ አበባ አስተዳደር ጤና ቢሮ፣ ደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ጤና ቢሮ፣ ኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጤና ቢሮ ቁጥጥር ለማድረግ ዕቅድ ቢይዙም በዕቅዱ መሰረት ያልተሰራ መሆኑ ታውቋል፡፡
24. ይህንኑ በተመለከተ የኦሮሚያ ጤና ቢሮ የሥራ ሂደት ባለቤት፣ የደቡብ እና የአዲስ አበባ ጤና ቢሮ የጤና ተቋማትና ባለሞያዎች የብቃት ማረጋገጥና ቁጥጥር ተ/ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ ቁጥጥርና ክትትል በሚያስፈልጋቸው ተቋማት በመገኘት ቁጥጥርና ክትትል ለማድረግ በዕቅድ ቢያዝም በጤና ተቋማት ቁጥር መብዛት፣ በሰው ኃይል እጥረት፣ በግብዓት እጥረት በመሳሰሉት ምክንያቶች በዓመት አንዴ ብቻ ቁጥጥር ማድረጋቸውን ሆኖም በስራቸው ያሉ ዞንና ወረዳዎች ቁጥጥርና ክትትል የሚያከናውኑ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ሆኖም ዕቅድ የሚያዘው የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድን ለብቻ ለማየት ሳይሆን አጠቃላይ የጤና ተቋማቱን አሰራር ለመከታተል ሲሆን በዛው ተካቶ የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ የሚታይ መሆኑን ገልፀዋል፡፡
25. በተጨማሪ በጤና ተቋማት ቁጥጥርና ክትትል ለማድረግ በሚሄዱበት ጊዜ የተገኙ ድክመቶችን ቀለል ያሉትን እንዲያስተካክሉ በቃል የሚነገራቸውና ከፍተኛ ድክመቶችን በፅሁፍ የሚያደርሷቸው መሆኑን እና በዞንና በወረዳ በሚደረጉ ቁጥጥሮች ጊዜ የሚገኙ ድክመቶች በቃል ብቻ የሚነግሯቸው ሲሆን ይህም የክልል ጤና ቢሮው ክትትል የሚያደርገው በዓመት አንዴ በናሙና በተመረጡት ላይ ብቻ በመሆኑ የጤና ተቋማቱ ትኩረት ሰጥተው የቆሻሻ አያያዙና አወጋገዱን እንዳይሰሩ ያደርጋል፡፡

26. የባለስልጣን መ/ቤቱ ም/ዋና ዳይሬክተር ተጠይቀው በሰጡት መልስ የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድን ለመቆጣጠርና ለመከታተል በዕቅድ የሚያዝ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ሆኖም የግል የጤና ተቋማትን ለመቆጣጠርና ለመከታተል የተያዘ ዕቅድ አለመኖሩን፡- ከ1999-2003 ዓ.ም በተዘጋጀው የአምስት ዓመት እስትራቴጂክ ዕቅድ እና በ2004 በጀት ዓመት ዕቅድ ላይ ያልተያዘ መሆኑ፣ በ2004 ዓ.ም የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ በግል የጤና ተቋማት ላይ የተሰሩ ስራዎች አለመታየታቸው እና በሐያትና በቤቴል ቲቺንግ ሆስፒታሎች በመገኘትም በተደረገው ቃለ መጠይቅ አጠቃላይ የሆስፒታሉን ስራ ቁጥጥር ለማከናወን ከባለስልጣን መ/ቤቱ በ2004 ዓ.ም አንድ ጊዜ ብቻ መገኘታቸውና የቆሻሻ አያያዙን በተመለከተ በፅሁፍ/በሪፖርት/ የተሰጠ መረጃ አለመኖሩ ታውቋል፡፡

27. ይህም የሚያሳየው በግል የጤና ተቋማት የቆሻሻ አያያዝና አወጋገዱ ላይ የቁጥጥርና የክትትል ሥራው በተጠናከረ ሁኔታ አለመደረጉና ትኩረት አለመሰጠቱን ሲሆን ከጤና ተቋማት የሚወጡ ቆሻሻዎች ስርዓት ባለው መልኩ ካልተያዙና ካልተወገዱ በሽታዎችን የሚያስተላልፉ በመሆናቸው ባለስልጣን መ/ቤቱ ባለድርሻ አካላትን በማስተባበር የመቆጣጠርና የመከታተል ሥራውን በተጠናከረ መልኩ ማከናወን እንደሚገባው ነው፡፡

<u>የህክምና ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድን በተመለከተ መመሪያዎች የወጡና ለጤና ተቋማት የደረሱ መሆኑን በተመለከተ</u>

28. ከጤና ተቋሞች የሚወጡ ቆሻሻዎች አያያዝና አወጋገድ በተመለከተ በሚኒስትር መ/ቤቱ እና በባለስልጣኑ መመሪያ ሊዘጋጁና ለጤና ተቋማት ሊደርሱ ይገባል፡፡ ባለሥልጣኑም በመመሪያው መሰረት መተግበሩን ክትትልና ቁጥጥር ሊያደረግ ይገባል፡፡

29. በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የተዘጋጀ የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ መመሪያ ቢኖርም በናሙና ተመርጠው የታዩ በአዲስ አበባ፣ በደቡብ እና በኦሮሚያ ክልል ለሚገኙ 42 የግል የጤና ተቋማት በሙሉ መመሪያው ያልደረሳቸው መሆኑ ታውቋል፡፡ /በኦዲቱ በናሙና የታዩት የጤና ተቋማት ስም ዝርዝር በአባሪ 2 ተያይዟል/፡፡

30. መመሪያ ያልደረሳቸው የጤና ተቋማት ስራቸውን በምን መሠረት እንደሚያከናውኑ ተጠይቀው በሰጡት መልስ ባላቸው ዕውቀት፣ በተለያየ ጊዜና ቦታ ከተቋሙ ውጪ ባገኙት ስልጠና፣ ከፍተኛ ክሊኒኮች እና መካከለኛ ክሊኒኮች ሲከፈቱ ሊያሟሉ የሚገባቸውን ዝርዝሮች የሚጠቅሰውን ስታንዳርድ በመጠቀም ሥራቸውን የሚያከናውኑ መሆናቸውን ለኦዲት ቡድኑ የመስክ ጉብኝት ባደረገበት ወቅት ገልፀዋል፡፡

31. ይህን በተመለከተ በኦሮሚያ ክልል የአዳማ ጤና ቢሮ የአካባቢ ቁጥጥር እና ፅዳት ኃላፊ እና የአዲስ አበባ ጤና ቢሮ የጤና ተቋማትና ባለሞያዎች ብቃት ማረጋገጥና ቁጥጥር ተ/ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ መመሪያ ያልደረሳቸው፣ በሆስፒታሎችም ሆነ በክሊኒኮች ለቁጥጥር በሚሄዱበት ጊዜ የሚጠቀሙት አዲስ የሚከፈቱ የጤና ተቋማት በሚከፈቱበት ጊዜ የቆሻሻ አያያዝና አወጋገዱን በተመለከተ ማሟላት ያለባቸው ነገሮችን በሚገልፀው ስታንዳርድ መሰረት መሆኑን ገልፀዋል፡፡

32. የባለስልጣን መ/ቤቱ ም/ዋና ዳይሬክተር መመሪያ ለግል የጤና ተቋማት ያልደረሰበት ምክንያትን ተጠይቀው በሰጡት መልስ የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ላይ በባለስልጣን መ/ቤቱ እየተዘጋጀ ያለ መመሪያ መኖሩን ሆኖም ቅድሚያ የጤና ተቋማት ሲከፈቱ ማሟላት ያለባቸው ነገሮችን የሚገልፅ አዲስ ስታንዳርድ በመዘጋጀት ላይ ያለ በመሆኑና ቅድሚያ ሊሰጠው ስለሚገባ በስታንዳርድ ዝግጅት ላይ በማተኮራቸው ምክንያት አዲሱ የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ መመሪያ ያልወጣ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

33. ይህም በመሆኑ በናሙና ተመርጠው በኦዲቱ በታዩ የጤና ተቋማት የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድን በተመለከተ የሚሰሩት ሥራዎች ወጥ በሆነ አሰራር ስርዓት መሰረት አለመሆኑ ታውቋል፡፡ ለምሳሌ መርፌዎች አገልግሎት ከሰጡ በኋላ የሚወገዱበት አንድ ዓይነት/ወጥ/ የሆነ አሠራር በየተቋማቱ አለመኖሩ በናሙና ባየናቸው ጤና ተቋማት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በአዳማ ከተማ መድህን ከፍተኛ ክሊኒክ እና በወላይታ ሶዶ ከተማ በእንያት ከፍተኛ ክሊኒክ መርፌው በቶሎ ተቃጥሎ አመድ የመሆን ፀባይ ስለሌለው መርፌውን በመንቀልና ለብቻው የሚወገድበት መንገድ በማዘጋጀት የሚጠቀሙ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ሌላው ደግሞ አሰላ ከተማ ውስጥ ዶ/ር አሸብር ሱራፌል ከፍተኛ ክሊኒክ ከወረዳ ለቁጥጥር በመጡ አካላት መርፌውን ከነሲሪንጁ ጉድጓድ ውስጥ አጠራቅሙ ተብለው በማጠራቀም ላይ መሆናቸውን፣ ጉድጓዱ ሊሞላ ትንሽ የቀረው መሆኑን፣ ጉድጓድ ውስጥ ያጠራቀሙት በዞኑ ጤና ቢሮ ትዕዛዝ መሰረት መሆኑን፣ ጉድጓዱ ሲሞላ ምን እንደሚያደርጉ ወደፊት እንደሚገለጽላቸው እና ጉድጓዱ እየሞላ በመሆኑ ምን ማድረግ እንዳለባቸው አለማወቃቸውን ገልፀዋል፡፡ በሌሎቹ በናሙና በታዩት ደግሞ ከነሲሪንጁ ከሌሎች ቆሻሻዎች ጋር በመደባለቅ በማቃጠያ ውስጥ የሚያቃጥሉ መሆኑን፣ ምክንያቱም ምንም አማራጭ የሌለና መወገድም ያለበት በዚህ ብቻ በመሆኑ ነው በማለት ገልጸዋል፡፡

34. ከዚህም በተጨማሪ ለቆሻሻ ማጠራቀሚያ የሚያገለግሉ ዕቃዎች በከለር ተለይተው መቀመጥ ሲገባቸው በከለር የማይለዩ፣ በሰውና በእንስሳት ላይ በሽታን የሚያስተላልፉ አደገኛ ቆሻሻዎች ላይ አለም አቀፍ የማስጠንቀቂያ የአደገኛነት ምልክት የማይደረጉ መሆናቸው፣ የቆሻሻ ማቃጠያዎች /ኢንስሌሬተሮች/ ወጥ የሆነ አሰራር የሌላቸው መሆናቸው ታውቋል፡፡

<u>በጤና ተቋማት ለሚሰሩ የፅዳት ሰራተኞችና ሌሎች ባለሙያዎች የሚሰጡ ስልጠናዎችን በተመለከተ፣</u>

35. ከህክምና ተቋማት የሚወጡ ቆሻሻዎች አደገኛነት አንፃር በጤና እና በአካባቢ ላይ የሚያስከትሉት ተፅዕኖ በተመለከተ በጤናው ዘርፍ ለተሰማሩ የጽዳት ሰራተኞች ሆነ ሌሎች ጉዳዩ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለሚመለከታቸው ሠራተኞች የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተከታታይነት ባለው መልኩ የሚሰጥበት ስርዓት በጤና ቢሮዎችም ሆነ በየጤና ተቋማት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

36. ሆኖም በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩት የግል የጤና ተቋማት ውስጥ ለሚሰሩ የፅዳት ሰራተኞችና ሌሎች ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ሠራተኞች የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተከታታይነት ባለው መልኩ የማይሰጣቸው ሲሆን በፅዳት ስራ ላይ የተሰማሩ ሠራተኞች ሥራቸውን የሚሰሩት ሲቀጠሩ በቃል በተሰጣቸው ኦሬንቴሽን ብቻ መሆኑ ታውቋል፡፡

37. የሜዲካል ቆሻሻ በሚመነጭበት የሕክምና መስጫ እና ታካሚ መኝታ ክፍሎች እና ላቦራቶሪዎች ውስጥ የሚሰሩ ሞያተኞችና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች እንዲሁም በአስተዳደርና ቁጥጥር ስራ ላይ የተሰማሩ የጤና ተቋማት ሠራተኞች ቋሚ በሆነ የጊዜ ሰሌዳ መሰረት የግንዛቤ ማዳበሪያ ትምህርት እንዲያገኙ ያልተደረገ መሆኑ፣ ለሐኪሞች፣ ለነርሶች፣ ለላብራቶሪ ቴክኒሺያኖችና ለፋርማሲስቶች ሜዲካል ቆሻሻን ከምንጩ/ከመነሻው/ ለመቀነስ የሚያስችሉ ዘዴዎችንና በአጠቃቀምና አያያዝ ላይ ሊደረግ የሚገባውን ጥንቃቄ እና ያለባቸውን ኃላፊነት እንዲያውቁት ለማድረግ የሚያስችል የተዘረጋ ሥርዓት አለመኖሩ ታውቋል፡፡

38. ይህን በተመለከተ የአዲስ አበባ ጤና ቢሮ የጤና ተቋማትና ባለሞያዎች ብቃት ማረጋገጥና ቁጥጥር ተ/ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ በግል የጤና ተቋማት ሰራተኞች ሲቀጠሩ ምን ምን መስራት እንዳለባቸው በጤና ተቋማቱ በኩል የሚነገራቸው መሆኑንና በበሽታ

መከላከል (Infection prevention) በሚሰጡ ስልጠናዎች ላይ ከሁሉም ተቋማት አንድ አንድ ሰው በመውሰድ ስልጠና እንደሚያገኙና የሰለጠነውም ሰው ወደራሱ ተቋም ወርዶ የሚያስተላልፍ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ የኦሮሚያ ክልል ጤና ቢሮ የሥራ ሂደት ባለቤትም በግል የጤና ተቋማት ለሚሰሩ የፅዳት ሰራተኞች የቆሻሻ አያያዝን በተመለከተ መደረግ ስላለባቸው ጥንቃቄዎች ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ ለሁሉም ማዳረስ ባይቻልም ለወደፊት ትኩረት ተሰጥቶት የሚሰራ መሆኑን አስታውቀዋል፡፡

39. የባለስልጣን መ/ቤቱ ም/ዳይሬክተርም ተጠይቀው በሰጡት መልስ በቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ላይ ስልጠናዎች የሚያስፈልግ መሆኑን በመግለፅ ነገር ግን በበጀት፣ በሰው ኃይል በመሳሰሉት ምክንያቶች አለመሰጠታቸውን እና ለወደፊትም በራሳቸው በጤና ተቋማቱ ሠራተኞችን የማፍራትና የማሰልጠን ስራ እንደሚሰራ ገልፀዋል፡፡

40. በግል የጤና ተቋማት የሚሰሩ የፅዳት ሰራተኞች የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስራ የሚሰሩት በጤና ተቋማቱ ሲቀጠሩ አንድ ጊዜ ብቻ በቃል በተነገሯቸው፣ በፊት ይሰሩበት ከነበሩባቸው ተቋማት ባገኙት ዕውቀት እና የፅዳት ኃላፊዎች/ሳኒቴሪያል/ በሚሰጧቸው መመሪያ/ትእዛዝ/ መሰረት መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ይህም ስልጠና በተቋማቱ፣ በጤና ቢሮ እና በባለስልጣን መ/ቤቱ የማይዘጋጁና የማይሰጡ መሆኑን በግል የጤና ተቋማት የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ትኩረት ተሰጥቶት የማይከናወን መሆኑን ያሳያል፡፡

**<u>ከግል የጤና ተቋማት የሚወጡ ቆሻሻዎች የሚወገዱበት የቆሻሻ ማቃጠያ/ኢንስሌሬተር/ ደረጃውን ጠብቀው የተሰሩ መሆናቸውን በተመለከተ፣</u>**

41. በግል የጤና ተቋማት የጤና አገልግሎት ከሚሰጥባቸው ክፍሎች የሚወጡ ቆሻሻዎች ማጠራቀሚያና ማቃጠያ /ኢንስሌሬተር/ በሁሉም የጤና ተቋማት ደረጃውን በጠበቀ መልኩ መሰራትና አገልግሎት መስጠት አለባቸው፡፡ የሚሰሩት የቆሻሻ ማቃጠያዎች ወጥነት ሊኖራቸውና ህክምና ከሚሰጥበትና ምግብ ከሚበስልበት አካባቢ 30 ሜ መራቅ አለባቸው፡፡

42. ሆኖም በናሙና ተመርጠው በኦዲቱ በታዩ የግል ጤና ተቋማት ውስጥ የተሰሩት የቆሻሻ ማጠራቀሚያና ማቃጠያዎች ወጥነት የሌላቸው ማለትም አንዳንዶቹ ትልቅ፣ ትንሽ፣ በራቸው ጠባብ እና ቆሻሻን ለመገልበጥ የማይመቹ፣ የጪስ ማውጫቸው አጭርና ረዥም የሆኑ ናቸው፡፡ በአዳማ ከተማ አዳማ ሆስፒታል የተሰራው የቆሻሻ ማቃጠያ ትልቅ ቢሆንም አጠቃቀሙን ካለማወቅና ከቸልተኝነት ቆሻሻው መቃጠል ከነበረበት ከላይኛው ክፍል

ውጪ በታችኛው ክፍል እና ከማጠራቀሚያው ውጪ ሲቃጠል በኦዲቱ ወቅት ታይቷል፡፡ ይህንንም በተመለከተ ለምን በማቃጠያው በስርዓት እንደማይጠቀሙ በዕለቱ ሲያቃጥሉ የነበሩት ሰራተኛ ተጠይቀው ሲያስረዱ ማቃጠያው ውስጥ አመዱ ባለመጠረጉና የላይኛው ማቃጠያ ላይ አመዱን ወደ ታች የሚያወርደው ወንፊት በመደፈኑ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ በዚሁ ከተማ ተክሌ ጨለሞ ከፍተኛ ክሊኒክ ቆሻሻ ለማቃጠል የሚሆን ኢንስሌሬተር የሌለና በጉድጓድ የሚጠቀሙ መሆኑን፣ በአዋሳ ከተማ አሰፋ ጉበዜ መታሰቢያ ክሊኒክ እና በወላይታ ሶዶ አዲስ ጤና መካከለኛ ክሊኒክ ውስጥ ለቆሻሻ ማጠራቀሚያ ማቃጠያ የሚሆን ኢንስሌተር ባለመሰራቱ በርሜል ቆርጠው የሚጠቀሙ መሆኑ ታይቷል፡፡

43. በአዲስ አበባ በላንድ ማርክ ሆስፒታል ያለው ኢንስሌሬተር አነስተኛና ከሆስፒታሉ ካፍቴሪያ 30 ሜ ያልራቀ መሆኑ፣ በድንበሯ ሆስፒታል ማቃጠያው /ኢንስሌሬተሩ/ ትንሽ መሆኑን፣ የመስክ ምልከታ በተደረገበት ዕለት ሳይቃጠል በመቅረቱ ሞልቶ የታየ፣ የልብስ ንፅህና/እጥበት/ ከቆሻሻ ማጠራቀሚያና ማቃጠያው የራቀ መሆን ሲገባው የሚታጠበው ቆሻሻ ማቃጠያው አጠገብ መሆኑ እና ህክምና ከሚሰጥበት ክፍል 30 ሜ ያልራቀና በተጨናነቀ ቦታ መሆኑ፣ በቅድስተ ማርያም ከፍተኛ ክሊኒክ የተሰራው ማቃጠያ ትንሽ መሆኑና በቤቶች መካከል የተሰራ መሆኑን፣ በተክለሃይማኖት ሆስፒታል የቆሻሻ ማቃጠያው ቆሻሻን ለመገልበጥ በማይመች መልኩ የተሰራ መሆኑ፣ በዮርዳኖስ ሆስፒታል እና በኋላሸት ከፍተኛ ክሊኒክ ቆሻሻዎች ኢንስሌሬተሩ ውስጥ ሞልተው በመሬት ላይ በመዝረክረክ ሳይቃጠሉ መቀመጣቸው በኦዲቱ ወቅት ታይቷል፡፡



ፎቶ 1 በአዲስ አበባ የሁልእሸት ከፍተኛ ክሊኒክ ቆሻሻዎች በማጠራቀሚያ ተዝረክርከው መቀመጣቸው የሚያሳይ ፎቶ



ፎቶ 2 በድንበሯ ሆስፒታል አነስተኛ የሆነ፣ የልብስ ንፅህና በአጠገቡ የሚሰጥበትና ቆሻሻው የሞላ ማቃጠያ የሚያሳይ ፎቶ

44.

45.



ፎቶ 3 በአዳማ ከተማ አዳማ ሆስፒታል ከማቃጠያ ውጪ ቆሻሻዎች ሲቃጠሉ የሚያሳይ



ፎቶ 4 በተክለሐይማኖት ሆስፒታል ቆሻሻን ለመገልበጥ ምቹ ያልሆነ የቆሻሻ ማቃጠያ የሚያሳይ



ፎቶ 5 በአዲስ አበባ በቅድስተ ማርያም ከፍተኛ ክሊኒክ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ በቤቶች መሐከልና ሞልቶ የሚያሳይ

46. በኪዩርና በቅዱስ ገብርኤል ሆስፒታል በኤሌክትሪክና በነዳጅ የሚሰሩ ዘመናዊ የቆሻሻ ማቃጠያዎች የጀመሩና ይህም ቆሻሻዎች በጤና ላይ ከሚያስከትሉት ጉዳት ለመከላከልና መርፌዎችን ለማቃጠልና ወደ አመድነት ለመቀየር በቂ ሙቀት ያላቸው በመሆናቸው ጥሩ ዘዴ ሆነው ታይተዋል፡፡ ነገር ግን በሌሎች በናሙና ተመርጠው በኦዲቱ በታዩ የግል የጤና ተቋማት የሚሰሩ የቆሻሻ ማቃጠያዎች አገልግሎት የሰጡ መርፌዎችን ለማቃጠል የሚበቃ ሙቀት/ኃይል/ ያላቸው መሆን ሲገባቸው ባለመሆናቸው አገልግሎት የሰጡ መርፌዎች በደንብ ሳይቃጠሉና ወደ አመድነት ሳይቀየሩ የሚቀሩና አመዱም ከሌሎች ቆሻሻዎች ጋር ተወስደው በከተሞች የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ጋር አብሮ የሚደፋ መሆኑ ታውቋል፡፡

47. የኦዲት ቡድኑ በተቋማቱ በላንድ ማርክ፣ በድንበሯ ሆስፒታሎችና በቪዠን፣ በቅድስት ማርያም፣ እንያት ከፍተኛ ክሊኒኮች በተዘዋወረበት ወቅት የተሰሩት የቆሻሻ ማቃጠያዎች ለምን አነስተኛ እንደሆኑ እና ህክምና ከሚሰጥበትና ምግብ ከሚበስልበት አካባቢ 30 ሜ እንዳልራቁ ተጠይቀው ተቋማቱ ሲገልጹ፤ አብዛኛው የግል ተቋማት የሚሰሩት አነስተኛ ቦታ ላይ በመሆኑ በቦታ ጥበት ምክንያት መሆኑን አስረድተዋል፡፡ በተክሌ ጨለሞ/አዳማ/ ከፍተኛ ክሊኒክ ቆሻሻን በጉድጓድ ለምን እንደሚያጠራቅሙና የቆሻሻ ማቃጠያ /ኢንስሌሬተር/ ለምን እንዳልሰሩ ተጠይቀው ሲያስረዱ የጤና ተቋሙ አነስተኛና ቆሻሻ የማይበዛ በመሆኑ፣ የቆሻሻ ማቃጠያ/ኢንስሌሬተር/ እንዲሰሩም ማንም አካል የጠየቃቸው ባለመኖሩና በቂ ነው ብለው በማመናቸው መሆኑን፣ አሰፋ ጉበዜ መታሰቢያና አዲስ ጤና መካከለኛ ክሊኒኮች ተቋማቱ አዲስ የተከፈቱ በመሆናቸው በርሜል በመቁረጥ የሚጠቀሙ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

48. የቆሻሻ ማቃጠያ አሰራርን በተመለከተ የአዳማ ጤና ቢሮ የአካባቢ ቁጥጥርና ፅዳት ሠራተኛ ተጠይቀው በሰጡት መልስ ተቋማቱ የሚሰሩት እንደአቅማቸው በመሆኑና በሂደት ይስተካከላል በማለት የሚሰሩ መሆኑን፣ የኦሮሚያ ጤና ቢሮ የሥራ ሂደት ባለቤት ደግሞ የግል የጤና ተቋማት ከየተቋማቸው የሚወጡ ቆሻሻዎችን በአግባቡ መያዝ እና ማስወገድ ላይ ያላቸው ግንዛቤ አናሳ በመሆናቸው ሲሆን በየአካባቢው ለሚገኙ ተቋማት አንድ ማዕከላዊ የሆነ ቦታ የሚዘጋጅበትና አግባብ ያለው የቆሻሻ አወጋገድ ስርዓት እንዲዘረጋ ስራዎች እየተሰሩ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

49. የአዲስ አበባ ጤና ቢሮ የጤና ተቋማትና ባለሞያዎች ብቃት ማረጋገጥ ቁጥጥር ተ/ኃላፊ ስለሁኔታው ተጠይቀው በሰጡት መልስ ለቆሻሻ ማቃጠያ የሚሰሩ ማቃጠያዎች

የአካባቢውን ብክለት ለመጠበቅ የጪስ ማውጫውን ከፍ አድርገው እንዲሰሩ ይደረጋል በማለት ገልፀዋል፡፡

50. በጤና ተቋማት የሚሰሩ የቆሻሻ ማቃጠያዎች አንድ ወጥ አለመሆናቸው፣ ቆሻሻን ለመገልበጥ የማያመቹ፣ ከተቃጠለም በኋላ አመዱን ለማውጣት የማያስችል፣ አመዱም ተጠርጐ በማውጣት ለብቻው በጉድጓድ አለመቀበሩ እና የህክምና አገልግሎትና ምግብ ከሚዘጋጅበት ክፍል 30 ሜ አለመራቁ ብክለትን ከመከላከል አንፃር ተገቢ ያልሆነ አሠራር ነው፡፡

<u>ለቆሻሻ ማስወገጃ የሚያገለግሉ ማቴሪያሎች በጤና ተቋማት መሟላታቸውን በተመለከተ፣</u>

51. በየጤና ተቋማት ለቆሻሻ ማጠራቀሚያ ሊያገለግሉ የሚችሉ የቆሻሻ ማጠራቀሚያዎች በየክፍሉ፣ በየኮሪደሩና በቆሻሻ ማጠራቀሚያ ቦታዎች ሊሟሉና ቆሻሻዎች በዓይነታቸው ተለይተው ወደ ማስወገጃ ቦታ ሊወሰዱና ሊወገዱ ይገባል፡፡ ይህንንም በተመለከተ ባለስልጣን መ/ቤቱም ሆነ የክልል ጤና ቢሮዎች ቁጥጥርና ክትትል ሊያደርጉ ይገባል፡፡

52. በኦዲቱ ወቅት በግል የጤና ተቋማት በናሙና በተመረጡ ሆስፒታሎችና ከፍተኛ ክሊኒኮች በተደረገው የመስክ ጉብኝት፡- በአዲስ አበባ በኪዮር ሆስፒታል በህክምና መስጫ ክፍሎችም ሆነ በየኮሪደሩ ለቆሻሻ ማጠራቀሚያ የሚሆኑና በከለር የተለዩ ማጠራቀሚያዎች፣ ቆሻሻዎችን ወደ ሚወገዱበት ቦታ መውሰጃ ጐማ ያለው /ትራንስፖርት/ ማቴሪያል የተዘጋጁ መሆኑ ታውቋል፡፡ በዮርዳኖስ ሆስፒታል የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ዕቃዎቹን ቀለም በመቀባት ለመጠቀም ቢጀምሩም ቀለሙ እየለቀቀ በመቸገራቸው በከለር/በቀለም/ እንደማይጠቀሙ ገልጸዋል፡፡ ነገር ግን በዩርዳኖስ ሆስፒታል፣ ቤተዛታ ሆስፒታል እና ሰናይ ከፍተኛ ክሊኒክ አደገኛና በሽታን የሚያስተላልፉ የሚባሉ የቆሻሻ ዕቃዎች ላይ (infections waste) በማለት በፅሑፍ ፅፎ ዕቃዎቹ ላይ በመለጠፍ እየተጠቀሙ መሆናቸውን በኦዲቱ ወቅት ታይቷል፡፡

53. ይሁን እንጂ በሌሎቹ በናሙና በታዩት የጤና ተቋማት የቆሻሻ ማጠራቀሚያዎች በከለር ያልተለዩ መሆናቸው ማለትም አደጋን የማያስከትሉ በጥቁር ከለር፣ አደገኛና በሰውና በእንስሳት ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ከደም ጋር ንክኪ ያላቸውና ስለታማ የሆኑ ነገሮች በቢጫ ከለር እና አደገኛ ብረት አዘል ንጥረነገሮች (heavy metals) በቀይ ከለር በተለዩ ማስቀመጫ ዕቃዎች ተለይተው መቀመጥ ሲኖርባቸው በከለር ያልተለዩ መሆናቸው በኦዲቱ ወቅት ታይቷል፡፡

54. በናሙና በኦዲቱ ተመርጠው የመስክ ጉብኝት በተደረገበት ወቅት ለምን የቆሻሻ ማጠራቀሚያዎችን በከለር ለይተው (color coding) እንደማይጠቀሙ በናሙና የተመረጡ የግል ጤና ተቋማት ባለሙያዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ ቢጫ፣ ጥቁርና ቀይ ቀለም ያላቸው የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ዕቃዎች በገበያ ላይ ማግኘት ባለመቻላቸው እንደሆነና አንዳንዶቹም ቆሻሻዎች በዓይነት ተለይተው ከተቀመጡ ችግር የለውም በሚል የግንዛቤ እጥረት ምክንያት መሆኑን ገልፀዋል፡፡

55. የደቡብና የኦሮሚያ ጤና ቢሮ የጤና እና ጤና ነክ የስራ ሂደት ባለቤትና የአዳማ ዞን የአካባቢ ቁጥጥርና ፅዳት ሠራተኛ ይህን በተመለከተ ተጠይቀው በሰጡት መልስ በግንዛቤ ማነስና ትኩረት ባለመስጠት ምክንያት መሆኑንና ወደፊት የሚስተካከል እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ የአዲስ አበባ ጤና ቢሮ የጤና ተቋማትና ባለሞያዎች ብቃት ማረጋገጥና ቁጥጥር ተ/ኃላፊ ስለጉዳዩ ተጠይቀው በሰጡት መልስ ለቁጥጥር በሚሄዱበት ጊዜ የከለር ኮድ የማይጠቀሙትን ተቋሞችን ያለመጠቀማቸውን በሚመለከቱበት ወቅት በከለር ለይተው እንዲጠቀሙ እንደሚነግሯቸው ገልፀዋል፡፡

56. ይሁን እንጂ በግል የጤና ተቋማት ውስጥ አገልግሎት የሰጡ መርፌዎች ማጠራቀሚያ የሚያገለግለው ሴፍቲ ቦክስ አጠቃቀምን በተመለከተ በኦዲቱ ወቅት በኦሮሚያ ክልል አዳማ ዞን መድህን ከፍተኛ ክሊኒክ መርፌዎች አገልግሎት ከሰጡ በኋላ በውስጡ ውሃ ያለውና አነስተኛ የሆነ መሳሪያ መርፌውን ለብቻው ነቅሎ በማስቀረት በቀናት ብዛት እየተበላ በመሄድ የሚወገድበት ዘዴና፣ በደቡብ ክልል ወላይታ ሶዶ ዞን እንያት ክሊኒክ መርፌዋን ለብቻ ነቅሎ ከፍተኛ ሙቀት ያለው ሚድል በርን በሚባል መሳሪያ የማስወገድ ስራ ሲጠቀሙ ታይቷል፡፡ እነዚህ ያገለገሉ መርፌዎችን የማስወገጃ ዘዴዎች በቆሻሻ ማስወገድ ስራ ላይ የተሰማሩ ሠራተኞችን በመርፌው ከሚደርስ ጉዳት ለመጠበቅ የሚያስችል መሆኑን በኦዲቱ ጊዜ የተገኙ ባለሞያዎች የገለፁ ሲሆን በሌሎች በናሙና ተመርጠው በታዩ የጤና ተቋማት በአዲስ አበባ ከቅዱስ ገብርኤል ሆስፒታል በስተቀር ሌሎቹ ሴፍቲ ቦክስ የሚጠቀሙ ቢሆንም በቂ ባለመሆኑ በተጨማሪ በካርቶን በማዘጋጀት፣ ወንፊታማ በሆነ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ውስጥ ላስቲክ ከውስጡ በማልበስ፣ የተጠራቀመውን መርፌ ወደ ቆሻሻ ማጠራቀሚያው በመገልበጥ ሴፍቲ ቦክሱን መልሰው መላልሰው በመጠቀም የሚገለገሉ መሆኑ ታውቋል፡፡ በቅዱስ ገብርኤል ሆስፒታል ደግሞ በሴፍቲ ቦክስም ሆነ በካርቶን በተሰራ የማይጠቀሙና ፕላስቲክ በሆነ ማቴሪያል የሚጠቀሙ መሆኑ ታይቷል፡፡

57. ከኘላስቲክ ከተሰራ ማቴሪያል መጠቀም ዕቃው ሲሞላ ከነመርፌው ስለማይቃጠል የፅዳት ሠራተኞች በሚገለብጡበት ወቅት መርፌው ጉዳት ሊያደርስባቸው ይችላል፡፡

58. በናሙና ተመርጠው በታዩ ሆስፒታሎች ሆነ በከፍተኛ ክሊኒኮች በተደረገ ጉብኝት ወቅት የተገኙት ባለሞያዎች መርፌዎችን በሴፍቲ ቦክስ ተጠቅመው ሶስት አራተኛ ሲሞላ ከነ ሴፍቲ ቦክሱ ወደ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ በመጣል ለምን እንደማያቃጥሉ ተጠይቀው በሰጡት መልስ ሴፍቲ ቦክስ በገበያ ላይ የማይገኝ መሆኑና ለግል የጤና ተቋማትም ከጤና ባለሞያዎች አካባቢ የሚሰጡት ቁጥራቸው አነስተኛ /በቁጥር 3 ወይም 4/ በመሆኑና ይህም በቂ ባለመሆኑ ምክንያት በካርቶን ማጠራቀሚያ በመስራትና ከነራሱ ማቃጠል ወይም ሴፍቲ ቦክሱን በመገልበጥ መልሶ የሚጠቀሙ መሆኑን፣ በተጨማሪ የግል የጤና ተቋማት ሴፍቲ ቦክሶችን ማሟላት ያለባቸው በግላቸው ነው የሚል አስተሳሰብ በመኖሩና ትኩረት ባለመሰጠቱ በበቂ ሁኔታ እንደማያገኙ ገልፀዋል፡፡







ፎቶ 6 ብዙ ጊዜ አገልግሎት የሰጠ ሴፍቲ ቦክስ የሚያሳይ

ፎቶ 7 በካርቶን የተዘጋጀ ሴፍቲ ቦክስ የሚያሳይ

59. የቅዱስ ገብርኤል ሆስፒታል የሐይጅንና አካባቢ ጤና አጠባበቅ ቴክኒሽያን ስለሁኔታው ተጠይቀው በሰጡት መልስ ሴፍቲ ቦክስ በገበያ ላይ እንደማይገኝና ቢገኝም እንኳን የአንዱ ዋጋ ውድ ሲሆን መጠቀም ያለባቸውም ብዙ በመሆኑ ካለው የወጪ አንፃር በኘላስቲክ በተሰራ ማጠራቀሚያ በማጠራቀምና ወደ ቆሻሻ ማቃጠያው በመገልበጥ የሚጠቀሙ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

60. የአዲስ አበባ ጤና ቢሮ የጤና ተቋማትና ባለሞያዎች ብቃት ማረጋገጥና ቁጥጥር ተ/ኃላፊ ይህን በተመለከተ ተጠይቀው በሰጡት መልስ ሴፍቲ ቦክስ ማዘጋጀት ያለባቸው እራሳቸው የግል የጤና ተቋማት መሆኑንና ለቁጥጥር በሚሄዱበት ጊዜ ሴፍቲ ቦክስ የማይጠቀሙትን በካርቶን አዘጋጅተው እንዲጠቀሙ ሙያዊ ምክር የሚሰጧቸው መሆኑን ገልፀዋል፡፡ የኦሮሚያ ክልል የሥራ ሂደት ባለቤትም ቁጥጥር በሚያደርጉበት ጊዜ ችግሩ ጉልቶ ያልታየ መሆኑንና ወደፊት ሴፍቲ ቦክስ ማግኘት የሚችሉበትን መንገድ እንደሚያመቻቹ ገልፀዋል፡፡

61. የባለስልጣኑ መ/ቤት ም/ዋና ዳይሬክተርም ስለሁኔታው ተጠይቀው በሰጡት መልስ እስካሁን ባለው ሂደት የሴፍቲ ቦክስ እጥረት እንዳለ የተገለፀላቸው ሁኔታ የሌለ መሆኑንና ችግር ካለም ከቢሮቻቸው ጋር በጋራ ከሚሰሩ ድርጅቶች ጋር ለመፍታት ጥረት ያደርጉ እንደነበር ገልፀዋል፡፡

62. አገልግሎት የሰጡ መርፌዎችን ማጠራቀሚያ /ሴፍቲ ቦክስ/ በግል የጤና ተቋማት በበቂ ሁኔታ ካልተሟላና በሴፍቲ ቦክስ የተጠራቀሙ መርፌዎችን ከነሴፍቲ ቦክሱ ካልተቃጠለ በሚገለበጡበት ጊዜ መርፌው በፅዳት ሠራተኞቹ ላይ ጉዳት ሊያደርስባቸው ይችላል፡፡

<u>በግል የጤና ተቋማት እና በጤና ቢሮዎች መካከል ስላለው የመረጃ ልውውጥ በተመለከተ</u>

63. ከጤና ተቋማት የሚወጡ /የሚወገዱ ቆሻሻዎችን በተመለከተ /የቆሻሻው ዓይነት፣ መጠን፣ የሚመነጩበት የስራ ክፍል፣ የሚቃጠሉበት ሰዓት … / በተመለከተ ተገቢው ሪከርድ/መረጃ የሚያዝበትና ሪፖርት የሚደረግበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ በግል ጤና ተቋማት ላይ የቁጥጥር እና ክትትል ስራ ከተሰራ በኋላ የግብረ መልስ ሪፖርት ለየጤና ተቋሙ እንዲሁም ደግሞ የጤና ተቋሙ ስራውን ስለማስተካከሉ በሪፖርት ለጤና ቢሮው ሊያሳውቅ ይገባል፡፡

64. በኦዲቱ በናሙና በተመረጡ ሆስፒታሎች፣ ከፍተኛ ክሊኒኮች እና መካከለኛ ክሊኒኮች የመስክ ስራ ወቅት በጤና ቢሮ የክትትል ስራ ስለመደረጉ ለማረጋገጫ እንዲሆን የቁጥጥር እና ክትትል ስራው ውጤት እና መስተካከል ስለሚገባቸው ነገሮች የሚገልፅ ደብዳቤ በጤና ቢሮዎች በኩል እንደማይሰጣቸው ከጤና ተቋማቱ ለማወቅ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም የግል ጤና ተቋማት የህክምና ቆሻሻን በተመለከተ የሚይዙትም ሆነ ለጤና ቢሮዎች የሚልኩት መረጃ እንደሌለ ለማወቅ ተችሏል፡፡

65. በአዳማ ከተማ የአዳማ ጤና ቢሮ የአካባቢ ቁጥጥር እና ፅዳት ኃላፊ ስለ መረጃ ልውውጥ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ቢሮው የሚጠቀምበት ፎርማት ያለው ሲሆን በዚሁ ፎርማት ላይ ያሉ ችግሮች ከተጠቀሱ በኋላ በማስፈረም በጤና ቢሮው ብቻ እንደሚቀር፣ መረጃውን በመተንተን ለሌላ ሥራ እንደማይጠቀሙበት ገልፀዋል፡፡ እንዲሁም በኦሮሚያ ጤና ቢሮ የሥራ ሂደት ባለቤት ስለ መረጃ ልውውጥ በተመለከተ ተጠይቀው በሰጡት መልስ ቁጥጥር በሚደረግባቸው የጤና ተቋማት በሙሉ የተገኘው ችግር በደብዳቤ እንደሚያሳውቁ ገልፀዋል፡፡ በደቡብ ብ/ብ/ህ/ክ ጤና ቢሮ የፈቃድ አሰጣጥ ኬዝቲም አስተባባሪና የቢሮ ኃላፊ ተወካይ ደግሞ የጤና ተቋማት የተላከላቸው ደብዳቤ ለማሳየት ፍቃደኛ ካለመሆን እንጂ የተገኙ ችግሮችን በደብዳቤ የሚያሳውቁ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ሆኖም የመስክ ስራው በተከናወነባቸው ሶስቱም ክልሎች የጤና ተቋማቱ ስራቸውን ማረማቸውን በሌላ ቁጥጥር ወቅት ከተሄደ የሚታይ እንጂ እርምጃ ስለመውሰዳቸው በደብዳቤ የሚያሳውቁበት መንገድ እንደሌለ ገልፀዋል፡፡

66. ይህ አካሄድም በተለያዩ የክልል ጤና ቢሮዎች፣ በስራቸው በሚገኙ ከተሞች በሚገኙ ጤና ቢሮዎች እና በግል ጤና ተቋማት መካከል ወጥ የሆነ የመረጃ ልውውጥ ስርዓት አለመኖሩን፣ በአንድ ክልል ውስጥም በሚገኙ የከተማ ጤና ቢሮዎች እና በክልሉ ጤና ቢሮ መካከልም የአሰራር ልዩነት መኖሩን የሚያሳይ ነው፡፡

67. በግል ጤና ተቋማት እና በጤና ቢሮዎች መካከል የቆሻሻ አወጋገድን አስመልክቶ የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት ቢኖር የግል ጤና ቢሮዎች በደብዳቤ በተገለፀላቸው መሰረት ስራቸውን ማከናወናቸውን፣ የተገኙባቸውን ችግሮች ማረማቸውን፣ ስራውን በምን ያክል ፍጥነት እንዳረሙ ለማረጋገጥ እና የተስተካከሉ ስራዎችን በትክክል ስለመከናወናቸው ክትትል ለማድረግ ያስችላል፡፡

**<u>የህክምና ቆሻሻን ለማስወገድ በግል የጤና ተቋማት ባለሙያ የተመደበ መሆኑን በተመለከተ</u>**

68. በግል የጤና ተቋማት በቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ላይ የሚሰሩ ሰራተኞች/ባለሞያዎች/ ሊመደቡና ለስራቸውም የስራ ኃላፊነትና ተግባራት በጽሑፍ ተዘጋጅቶ ሊደርሳቸው ይገባል:: ከህክምና ተቋማት የሚወጡ ቆሻሻዎች በጤና ባለሞያ ተለይቶ ሊወገድ ይገባል፡፡

69. በኦዲቱ ወቅት በተለያዩ የስራ ኃላፊዎች የጤና ተቋማት በስራቸው ማቋቋም ከሚገባቸው የስራ ክፍሎች ውስጥ የሳኒቴሽን እና ሃይጂን ባለሙያ አንዱ መሆኑን ተገልጿል፡፡ ሆኖም በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩ የግል የጤና ተቋማት ውስጥ በአዲስ አበባ

ከሚገኙት ሆስፒታሎች/ሐያት፣ ቤቴል፣ ተክለሐይማኖት፣ ላንድማርክ፣ ቅዱስ ገብርኤል/፣ በአዳማ ከተማ አዳማ አጠቃላይ ሆስፒታል እና በኦሮሚያ ክልል በአቅልሲያ መታሰቢያ ጠቅላላ ሆስፒታሎች በስተቀር በሌሎች በናሙና በታዩ ሆስፒታሎች፣ ከፍተኛና መካከለኛ ክሊኒኮች ውስጥ የሳኒቴሽን እና የሃይጂን ባለሙያ በመቅጠር የህክምና ቆሻሻዎች በዚሁ ባለሙያ እንዲለዩ አይደረግም፡፡ በተጨማሪም የህክምና ቆሻሻ የማፅዳት ስራ ተቀጥረው ለሚሰሩ የፅዳት ሰራተኞች ስራቸውን በሚመለከት በየተቋሙ የሚዘጋጁ የስራ መዘርዝር አለመኖሩን ለማወቅ ተችሏል፡፡

70. ስለሁኔታው በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልል ጤና ቢሮ የቁጥጥር ኦፊሰር ተጠይቀው በሰጡት መልስ በጤና ተቋማት የስራ መዘርዝር ተዘጋጅተው መለጠፍ ወይም መስጠት እንዳለባቸው፣ በአዲስ አበባ ክልል ጤና ቢሮ የጤና ተቋማትና ባለሞያዎች ብቃት ማረጋገጥ ቁጥጥር ተ/ኃላፊ ቀጣሪው መ/ቤቶች የሠራተኛን የስራ መዘርዝር አዘጋጅተው መስጠት ያለባቸው መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ነገር ግን ኃላፊዎቹ ይሄን ይበሉ እንጂ የስራ መዘርዝርን በተመለከተ በግል የጤና ተቋማት ውስጥ የሥራ መዘርዝር የሌለ መሆኑ በዚሁ ላይ ምንም ዓይነት የተደረገ ክትትልና ቁጥጥር የሌለ መሆኑና የተወሰደ እርምጃም እንደሌለ በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

71. የሳኒቴሽን እና ሃይጂን ባለሙያ በግል ጤና ተቋማቱ ያለመገኘትና የስራ መዘርዝር ተዘጋጅቶ አለመድረስ የህክምና ቆሻሻዎች በሚገባ በመለየት እና በሚቃጠሉበት ወቅትም ከፍተኛ ሙቀት የሚያስፈልጋቸውን እና የማያስፈልጋቸውን እንዲሁም መቃጠል የሚገባቸውን እና የማይገባቸውን ለምሳሌ ፕላስቲክ እና ራጅ የመሳሰሉትን ቆሻሻዎች በአንድ ላይ ወደ ኢንስለሬተር በመጨመር እና በማቃጠል በአካባቢ ብክለት ላይ ከፍ ያለ ተፅእኖ የሚያደርሱ እና እንደ መርፌ እና ስለታም የሆኑ መሳሪያዎችም በበቂ የሙቀት መጠን ባለመቃጠላቸው በሽታን ሊያስተላልፉ እንደሚችሉ ታውቋል፡፡

**<u>ከህክምና ተቋሙ የሚወጡ ቆሻሻዎች ከጤና ተቋሙ ከመውጣታቸው በፊት የብክለት ደረጃቸውን እንዲቀንሱ ተደርገው የሚወጡ መሆኑን በተመለከተ፣</u>**

72. ከህክምና ተቋማት የሚወጡ ስለታማ እና ጫፋቸው ሹል የሆኑ የህክምና ቁሶች በተገቢው ሙቀት ሊቃጠሉ ይገባል፡፡ ከህክምና ተቋማት የሚወጡ ፍሳሾች ህብረተሰቡ ከሚጠቀምባቸው ስፍራዎች ከመለቀቃቸው በፊት ሊታከሙ ይገባል፡፡

73. በናሙና ተመርጠው ከታዩ ሆስፒታሎች ውስጥ አንዱ በሆነው በአዲስ አበባ በቅዱስ ገብርኤል ሆስፒታል ከሆስፒታሉ የሚወጡ ፍሳሾች ደረጃውን በጠበቀ መልኩ ህክምና ከተደረገለት በኋላ በአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን የጉዳት ደረጃቸው ተመዝኖ ወደ አካባቢው እንዲለቀቅ የሚደረግ መሆኑን የገለፁልን ሲሆን፣ በቤቴል ቲቺንግ ሆስፒታል ከህክምና የሚወጡ ፍሳሾች የትም እንደማይለቀቁ እና ለባዮጋዝ ጥቅም እንደሚውሉ፣ በአሰላ ከተማ ዶ/ር አሸብር ሱራፌል እስፔሻል ክሊኒክ ውስጥ ከክሊኒኩ የሚወጡ ፍሳሾችን ህክምና ለመስጠት የሚያስችል ቦታና የሚያስፈልገውን ስራ በማዘጋጀት ወደፊት ለመስራት የተጀመረ ስራ ያለ መሆኑን የገለጹ ሲሆን በኦዲቱ ወቅትም ታይቷል፡፡

74. ከነዚህ የጤና ተቋማት ውጪ በናሙና የታዩት የግል የጤና ተቋሞች በውሃ እና ፍሳሽ ቢሮ በላቦራቶሪ የጉዳት መጠናቸው ከመመርመሩ በፊት ህብረተሰቡ በሚጠቀምባቸው አካባቢዎች ለምሳሌ በወንዞች እና በፍሳሽ ማስወገጃ ትቦዎች/በውሃና ፍሳሽ፣ በግለሰቦችና በተለያዩ ዘዴ እንደሚያስወግዱ ታውቋል፡፡ ስለታማ የሆኑ የህክምና ቆሻሻዎችም በናሙና ተመርጠው ከታዩት ውስጥ በኪዩር ጠቅላላ ሆስፒታልና በቅዱስ ገብርኤል ጠቅላላ ሆስፒታል ኢንስሌሬተሩ የሚሰራው በኤሌክትሪክ እና በነዳጅ ሃይል በመሆኑ ስለታማ ቁሶችም አብረው እንደሚቀልጡ የታየ ሲሆን በወላይታ ከተማ ከአንያት መካከለኛ ክሊኒክ በስተቀር በሌሎች በናሙና በተመረጡ የግል ጤና ተቋማት እነዚህ የህክምና ቆሻሻዎች በበቂ ሙቀት/አቅም/ ሳይቀልጡ ከጤና ተቋሙ ግቢ ውጭ እንደሚወገዱ ታይቷል፡፡

75. ይህንን በተመለከተ በናሙና ከተመረጡ የክልል ጤና ቢሮ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ በተሰጠው ምላሽ ፍሳሾች ወደ ወንዝ እና ህብረተሰቡ ወደሚደርስባቸው ስፍራዎች ከመለቀቃቸው በፊት በጤና ተቋማቱ ህክምና መደረግ እንደነበረባቸው ገልፀዋል፡፡ ስለታማ የሆኑ የህክምና ቆሻሻዎች ስለሚወገዱበት ሂደት ሲገልፁም ኢንስሌሬተሮች ውስጥ እርጥብ ነክ የሆኑ ቆሻሻዎች ስለሚጨመሩ ኢንስሌለሬተሩ በበቂ ሙቀት መርፌዎችና ጫፋቸው ሹል የሆኑ ቁሶችን እንዲቃጠሉ ማድረግ አለመቻሉን ገልፀዋል፡፡

76. የክልልም ሆኑ የከተማ የጤና ተቋማት የፍሳሽ አወጋገድን በተመለከተ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት በመስራት ከህክምና ተቋማት የሚወጡ ፍሳሾች ህብረተሰቡ በሚጠቀምባቸው ስፍራዎች ከመለቀቃቸው በፊት የብክለት መጠናቸው ታውቆና ታክሞ መለቀቅ ሲገባቸው ይህ ሳይሆን ወደ ህብረተስቡ መለቀቁ ለተለያዩ የበሽታ መስፋፋት መንስኤ በመሆን ህብረተሰቡን ሊጎዱ ይችላሉ፡፡

**የህክምና ቆሻሻ አወጋገድን በተመለከተ ከባለድርሻ አካላት ጋር በጋር የሚሰራበት ሁኔታ መኖሩን በተመለከተ፣**

77. ባለስልጣኑ እና የክልል ጤና ቢሮዎች የህክምና ቆሻሻን አያያዝና አወጋገድን በተመለከተ ከከተማ ማዘጋጃ ቤቶች እና ሌሎች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በጋራ የሚሰሩበትን የአሰራር ስርዓት ሊዘረጉ ይገባል፡፡

78. በናሙና ተመርጠው በታዩ የጤና ተቋማት እንደተገለፀው ከህክምና ተቋሙ የሚወጡ ቆሻሻዎች ከተቃጠሉ በኋላ አመዱ ከሌሎች ቆሻሻዎች ማለትም የሜዲካል ቆሻሻ ካልሆኑ ቆሻሻዎች ጋር ተደባልቀው ቆሻሻ ለሚያጓጉዙ አካላት በመስጠት የሚደፋ መሆኑን፣ አመዱ ከህክምና ተቋሙ ውጭ በሚደፋበት ጊዜ የሚደፋበት ቦታ ማዘጋጃ ቤቱ ለደረቅ ቆሻሻ ባዘጋጀው ቦታ ላይ በመሆኑ ይሄም የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ሊደርሱበት የሚችሉበትና የህክምና ቆሻሻዎች የተቃጠሉበት የሙቀት መጠን እና አመዱ ሊያመጣ የሚችለው የብክለት መጠን ስለማይታወቅ ለብቻው የማይቀበር መሆኑ፣ በኦዲት ወቅት ታይቷል፡፡

79. ስለሁኔታው የግል ጤና ተቋሞች ተጠይቀው በጤና ተቋሙ ግቢ ውስጥ ለመቅበርም ግቢው የሚገኝበት ቦታ ጠባብ በመሆኑና የአመድ መቅበሪያ ቦታ ለመቆፈር የማይቻል በመሆኑ ይሄን ችግር ለመፍታት ማዘጋጃ ቤት ከህክምና ቦታ ወጥተው የተቃጠሉ ቆሻሻዎችን አመድ መቅበሪያ ቦታ ቢያዘጋጅ መልካም መሆኑን የገለፁ ሲሆን ይሄ መሆን ባለመቻሉ ደረቅ ቆሻሻ በሚጣልበት ስፍራ የሚደፋ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

80. ይህንንም በተመለከተ የየክልል ጤና ቢሮዎችም ተጠይቀው በሰጡት መልስ በእስታንዳርዱ መሰረት አመዱም ቢሆን ከህክምና ተቋሙ ግቢ ውጭ መደፋት እንደሌለበት፣ የአመድ መቅበሪያ ቦታ ሊያዘጋጁ እና በዚሁ ሊጠቀሙ የሚችሉ መሆኑን የገለፁ ሲሆን የማዘጋጃ ቤትን በተመለከተ ግን የጤና ቢሮዎች ወደፊት እንደሚያስቡበት ገልፀዋል፡፡

81. የክልል ጤና ቢሮዎች አመዱ ከህክምና ተቋሙ ግቢ ውጪ መውጣት የለበትም ቢሉም ለግል የጤና ተቋማት ፍቃድ በሚሰጥበት ወቅት ሟሟላት ከሚገባቸው ነገሮች ውስጥ አንዱ የግቢው ስፋት እንደመሆኑ መጠን ለስራ የሚጠቀሙበት ግቢ እጅግ ከመጥበቡ የተነሳ የተቃጠለውን እና ወደ አመድነት የተቀየረውን ቆሻሻ ቆፍሮ ለመቅበር የሚያስችል የቦታ ስፋት እንደሌላቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡

82. ይህንንም በተመለከተ የባለስልጣን መ/ቤቱ ሃላፊዎች በኦዲት መውጫ ስብሰባ ወቅት በተደረገ ውይይት ችግሩን ለመቅረፍ ከአዲስ አበባ ከተማ ማዘጋጃ ቤት የተጀመሩ ስራዎች እንዳሉ እና መጠናከር እንዳለባቸው ገልፀዋል፡፡

83. በመሆኑም ይህ ሊሆን የቻለበት ምክንያት ባለስልጣን መ/ቤቱም ሆነ የክልል ጤና ቢሮዎች ከህክምና ተቋማት የሚወጡ ቆሻሻዎች በአንድ ላይ የሚወገዱበት መንገድን ለማመቻቸት ከባለድርሻ አካላት ጋር በተለይ ከማዘጋጃ ቤት ጋር በጋራ ለመስራት ምንም ዓይነት ስርዓት ባለመዘርጋቱ/አለመኖሩ/ እና ማዘጋጃ ቤትም ይህን በተመለከተ ምንም ያዘጋጀው ቦታ ባለመኖሩ ነው፡፡

84. በመሆኑም የሕዝብ ጤና የመጠበቅ፣ የአካባቢ ደህንነትን የማረጋገጥ እና በሽታን የመከላከል ኃላፊነት የጤናው ዘርፍ ዋነኛ ጉዳይ ሆኖ ለዚህ ትኩረት አለመሰጠቱ በሜዲካል ቆሻሻ አማካኝነት ሊከሰቱ የሚችሉ ችግሮችን ለመከላከል እና የህብረተሰቡን ጤና ለመጠበቅ፣ እንዲሁም በውሃ፣ በአየርና በአፈር ላይ የሚደርስ ብክለትን ለመከላከል የማያስችል መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

# ክፍል ሶስት

# መደምደሚያዎች

85. ከላይ በኦዲት ግኝቶች ላይ እንደተመለከተው በናሙና ተመርጠው በታዩ የግል የጤና ተቋሞች የህክምና ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድን በተመለከተ የሚከተሉት መደምደሚያዎች ተሰጥተዋል፡፡

- የግል የጤና ተቋማትን የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድን በተመለከተ ቁጥጥርና ክትትል ለማድረግ በባለስልጣን መ/ቤቱ ዕቅድ ያልተያዘ ሲሆን የአዲስ አበባ ከተማ፣ የኦሮሚያ፣ የደቡብ ሕዝቦች ብሔር ብሔረሰቦች ክልላዊ መንግስት ጤና ቢሮዎች በዕቅድ ቢያዝም በዕቅዱ መሰረት ያልተከናወነ መሆኑ፣
- የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድን በተመለከተ ባለስልጣን መ/ቤቱ በአዲስ ከተዋቀረበት ከ2002 ዓ.ም ጀምሮ መመሪያ እየተዘጋጀ ያለ ቢሆንም መመሪያውን በማጠናቀቅ ስራ ላይ እንዲውል ለግል የጤና ተቋማት ያልተሠራጨ መሆኑ፣
- ከሜዲካል ቆሻሻ ጋር ቀጥታ የሥራ ግንኙነት ላላቸው የፅዳት ሞያተኞች እና ለሌሎች ጉዳዩ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለሚመለከታቸው ሠራተኞች የሜዲካል ቆሻሻን አደገኛነት ጠባይና መደረግ ስለሚገባው ጥንቃቄ የሚሰጡ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎች የሌሉ መሆኑ፣
- በግል የጤና ተቋማት የሚሰሩ የቆሻሻ ማቃጠያዎች/ኢንስሌሬተርስ/ ወጥነት የሌላቸው መሆኑ፣
- በየህክምና ክፍሎች ለቆሻሻ ማጠራቀሚያ የተዘጋጁት ዕቃዎች በአለም አቀፍ ደረጃ እየተሰራባቸው በሚገኙ የቀለም አይነቶች (color coding) እንዲለዩ አለመደረጉ፣ በዚህም ምክንያት የአደገኛነት ጠባይ ያላቸው የሜዲካል ቆሻሻዎች ከሌሎች አደገኛነት ከሌላቸው ቆሻሻዎች ጋር ተቀላቅለው የሚሰበሰቡና የማጠራቀሚያ ገንዳዎች በሰዎች መተላለፊያ ቦታ ሣይከደኑ የሚቀመጡ መሆናቸው፣
- የግል የጤና ተቋማት ከባለስልጣን መ/ቤቱም ሆነ ከጤና ቢሮዎች ጋር የህክምና ቆሻሻን በተመለከተ የተጠናከረ የመረጃ ልውውጥ ስርዓት የሌላቸው መሆኑ፣
- በግል የጤና ተቋማት በአብዛኛው በከፍተኛና መካከለኛ ክሊኒኮች የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ የሚቆጣጠር/ሳኒቴሪያል/ ባለሞያ ያልተሟሉ መሆኑና ተቋማቱ ለሰራተኞች የስራ መዘርዝር አዘጋጅተው ያልሰጡ መሆኑ፣

- ከግል የጤና ተቋማት የሚወጡ የፍሳሽ ቆሻሻዎች ህክምና ሣይደረግላቸው/ሳይታከም/ ወይም የብክለት ደረጃቸው ሳይታወቅ ወደ ወንዞች እና አካባቢዎች የሚለቀቁ መሆኑ፣
- ከጤና ተቋማት የሚወጡ ቆሻሻዎችን በተመለከተ ከማዘጋጃ ቤቶች ጋር በጋራ የማይሰራ መሆኑ እና በህክምና ተቋማት የሚቃጠሉ ቆሻሻዎች አመድ ከሌሎች ቆሻሻዎች ጋር በተገኘው ቦታ የሚደፋ መሆኑ፣

ታውቋል፡፡

86. በአጠቃላይ ከላይ በተጠቀሱት ዋና ዋና ችግሮች ላይ እርምጃ ካልተወሰደ በሆስፒታሎችና በክሊኒኮች ያለው የሜዲካል ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ሥራ በወንዞች፣ በአፈርና በአየር ላይ ብክለት በማስከተል የሰውና የእንስሳት ጤና ሊያውኩ እና የተፈጥሮ ሃብት ላይ ጉዳት ሊያስከትል እንደሚችል ይገመታል፡፡ የጤና ተቋማት ቆሻሻን ከምንጩ ጀምሮ እስከሚወገድበት ድረስ ያለውን የሥራ ሂደት አካባቢን በማይበክል፣ የሰውና እንስሳት ጤናን በማይጐዳ መልኩ ማከናወን ሲገባቸው ይህ አለመደረጉ እና በስራው ላይ ለተሰማሩ ባለሞያዎችና ለሌሎች የግንዛቤ ማዳበሪያ ትምህርት የሚያገኙበት ሥርዓት አለመዘርጋቱ አግባብ አለመሆኑ ታውቋል፡፡
87. ስለሆነም ከላይ የተገለፁትን በኦዲት ወቅት የተገኙትን ግድፈቶች ለማስወገድ ወይም ለማቃለል አስተዋጽኦ ያደርጋሉ ተብለው የታሰቡ የማሻሻያ ሃሳቦችን በሚቀጥለው የሪፖርት ክፍል አቅርበናል፡፡

# ክፍል አራት

# የማሻሻያ ሀሳብ

88. ባለስልጣን መ/ቤቱ በስሩ ባሉና ፍቃድ በሚሰጣቸው የግል የጤና ተቋማት የህክምና ቆሻሻ አወጋገድን በተመለከተ ቁጥጥርና ክትትል ለማድረግ ዕቅድ የማዘጋጀት፣ በዕቅድ የተያዙ ስራዎችን ከባለድርሻ አካላት ጋር በመወያየትና የትብብር ስልት በመንደፍ መሰራታቸውን ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡ በተጨማሪ የክልል ጤና ቢሮዎችም ሆኑ የከተማ ጤና ጽ/ቤቶች የቆሻሻ አያያዝን በተመለከተ በዕቅድ የተያዙ ስራዎችን በተያዘላቸው ጊዜ ተገቢውን የአቅም ግንባታ ሥራ በመስራት ሊተገብሩ ይገባል፡፡

89. ከጤና ተቋማት የሚወጡ ቆሻሻዎች በአግባቡ ካልተያዙና ካልተወገዱ የሚያደርሱት አደጋ ከፍተኛ በመሆኑ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድን በተመለከተ እየተዘጋጀ ያለው መመሪያ ተጠናቆ በማውጣትና ከባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት ለጤና ተቋማት ሊደርስ እና ስራ ላይ ሊውል ይገባል፡፡ መመሪያው ለጤና ተቋማት መድረሱንና ስራ ላይ መዋሉን ባለስልጣን መ/ቤቱ ሊከታተልና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡

90. በግል የጤና ተቋማት ለሚሰሩ የፅዳትም ሆነ በሌላ ስራ ላይ ለተሰማሩ ሠራተኞች ከጤና ተቋማት የሚወጡ ቆሻሻዎች አያያዝ፣ አወጋገድና በአካባቢ ላይ የሚያስከትሉትን ተፅዕኖ በተመለከተ በጤና ተቋማቱ፣ በጤና ቢሮዎች እና በባለስልጣን መ/ቤቱ ስልጠናዎች ሊያዘጋጁና ሊሰጡ ይገባል፡፡ ባለስልጣን መ/ቤቱ የግል የጤና ተቋማት ሠራተኞች ስልጠና ማግኘታቸውንና በስልጠናው መሰረት መስራታቸውን ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡

91. ለሜዲካል ቆሻሻ ማቃጠያ የሚሰሩ ኢንስሌሬተሮች ወጥ የሆነ አሰራር /ደረጃ/ ሊኖራቸው ወይም በኤሌክትሪክ እና በነዳጅ ኃይል የሚሰሩ ኢንስሌሬተሮች ለቆሻሻ ማስወገድ ስራ ከፍተኛ ጠቀሜታ ስለሚኖራቸው እነዚህን መጠቀም እንዲቻል ከባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት በተመጣጠነ ዋጋ የሚያገኙበት መንገድ ሊመቻች ይገባል፡፡

92. ከጤና ተቋማት ለሚወጡ ቆሻሻዎች ማጠራቀሚያ፣ ማጓጓዣና ማስወገጃ የሚያገለግሉ መሣሪያዎች ሊሟሉና በየክፍሉ ለቆሻሻ ማጠራቀሚያ የሚያገለግሉ ዕቃዎችም በከለር ተለይተው አገልግሎት ሊሰጡ ይገባል፡፡ ይህም መሟላቱን ባለስልጣን መ/ቤቱም ሆነ የጤና ቢሮዎች ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርጉ ይገባል፡፡

93. ባለስልጣኑ የአዲስ አበባ ጤና ቢሮ እና የክልል ጤና ቢሮዎች በስራቸው ካሉ ከግል የጤና ተቋማት የሚወጡ ቆሻሻዎችን ቁጥጥርና ክትትል በተመለከተ ተገቢው የመረጃ ልውውጥ

ሥርዓት በተጠናከረ ሁኔታ እንዲኖራቸው ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡ ይህም የጤና ተቋማቱ ለቆሻሻ አያያዙና አወጋገዱ ትኩረት እንዲሰጡና እንዲሰሩ ያደርጋቸዋል፡፡

94. በግል የጤና ተቋማት የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስራ በኃላፊነት የሚሰራ ባለሙያ/ሳኒቴሪያል/ በሆስፒታሎችና በከፍተኛ ክሊኒኮች ሊሟሉ ይገባል፡፡ በፅዳት አገልግሎት ለተቀጠሩም ባለሞያዎች በተቋሞቹ የስራ መዘርዝር ተዘጋጅቶ ሊደርሳቸውና ስለተግባራዊነቱም ተቋሙና የጤና ቢሮዎች ክትትል ሊያደርጉ ይገባል፡፡
95. ከተቋማቱ የሚወጡ ፍሳሽ ቆሻሻዎች የብክለት ደረጃቸው ሳይለካ እንዳይለቀቁ የባለስልጣን መ/ቤቱም ሆነ የጤና ቢሮዎች ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርጉና ለተቋማቱም ይህን በተመለከተ ግንዛቤ እንዲያገኙና የልኬት መጠናቸውን ሳያስለኩ እንዳይለቁ የሚደረግበት መንገድ ሊዘረጋ ይገባል፡፡
96. ከህክምና ተቋማት የሚወጡ ቆሻሻዎች በአግባቡ ለመያዝና ለማስወገድ፣ በጤና ላይ ከሚያደርሱት ጉዳት ለመጠበቅ የጤና ቢሮዎች ከማዘጋጃ ቤቶች ጋር በቅንጅት በመስራት ከጤና ተቋማት የሚወጡ ቆሻሻዎች በአንድ ላይ የሚሆኑበትና የሚወገዱበት መንገድ ሊመቻች ይገባል፡፡

በመጨረሻም በኦዲቱ ወቅት የባለስልጣን መ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች፣ የአዲስ አበባ ጤና ቢሮ፣ የኦሮሚያ ጤና ቢሮ፣ በኦሮሚያ ክልል የአዳማ ጤና ጽ/ቤት፣ የደቡብ ክልል የጤና ቢሮ ኃላፊዎች እና ሠራተኞች እንዲሁም በኦዲቱ ወቅት መረጃ የሰበሰብንባቸው ሆስፒታሎች፣ ከፍተኛና መካከለኛ ክሊኒኮች ኃላፊዎች እና ሠራተኞች ስላደረጉልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡

## አባሪ 1

# የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች

**/Evaluative criteria /**

| ተ.ቁ | የኦዲትጭብጥ / ISSUES/ | የመመዘኛመስፈርቶች /EVALUATIVE CRITERIA/ |
|---|---|---|
| 1. | ከግል ተቋማት የሚወጡ ቆሻሻዎች አያያዝና አወጋገድን በተመለከተ መመሪያዎች ስለመኖራቸውና በጤናው ዘርፍ ለተሰማሩ ሠራተኞች ስልጠና መሰጠቱ እና ከባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ መተግበራቸውን ማጣራት፣ | 1.1 የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድን የሚከታተል ክፍል ለሚያከናውነው ተግባራት የረጅምና የአጭር ጊዜ ዕቅድ ሊያዘጋጅና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | | 1.2 ከግል የህክምና አገልግሎት መስጫ ተቋሞች የሚወጡ የቆሻሻዎችን አያያዝና አወጋገድ በተመለከተ መመሪያ ሊዘጋጅ ይገባል፡፡ |
| | | 1.3 የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድን በተመለከተ የሚዘጋጁ መመሪያዎች፣ ደንቦች የመሳሰሉት ለግል ሆስፒታሎችም ሆነ ለክሊኒኮች ሊሰራጩ ይገባል፡፡ |
| | | 1.4 ከግል የህክምና አገልግሎት መስጫ ተቋሞች ለሚወጡ ቆሻሻዎች የቆሻሻ ማቃጠያዎች ግንባታን የሚመለከት መመሪያ /መስፈርት ሊኖርና ስራ ላይ ሊውል ይገባል፡፡ |
| | | 1.5 የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ መመሪያ በሚዘጋጅበት ወቅት የግል የጤና ተቋማት ተሳታፊ ሊደረጉ ይገባል፡፡ |
| | | 1.6 በቆሻሻ አወጋገድ /በፅዳት/ ላይ ለተሰማሩ ሰራተኞች ለቆሻሻ አያያዝና አወጋገድን በተመለከተ በሚወጡ መመሪያዎች /ደንቦች/ መሰረት ስልጠና ሊሰጥ ይገባል፡፡ |
| | | 1.7 በቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ላይ የሚሰጡ ስልጠናዎች ተከታታይነት ሊኖራቸው ይገባል፡፡ |
| | | 1.8 ከህክምና ተቋማት የሚወጡ ቆሻሻዎች በጤና እና በአካባቢ ላይ የሚያስከትሉት ተፅዕኖ በተመለከተ በጤናው ዘርፍ ለተሰማሩ ሰራተኞች ስልጠና/የግንዛቤ ማስጨበጫ መስጠት አለበት፡፡ |

| | | |
|---|---|---|
| | | 1.9 የአካባቢ ደህንነትና ጤና ያላቸውን ትስስር፣ የሜዲካል ቆሻሻ በአካባቢ ደህንነትና ጤና ላይ የሚያስከትለውን ጉዳት እና መደረግ ስለሚገባው ጥንቃቄ የሚያስረዳ የትምህርትና ግንዛቤ ማዳበሪያ ማቴሪያሎች መዘጋጀት አለባቸው፡፡ |
| 2 | ከግል የጤና ተቋማት የሚወጡ ቆሻሻዎች አሰባሰብ፣ አያያዝ፣ አጓጓዝና አወጋገድ ስርዓት ባለው ሂደት፣ ባለስልጣን መ/ቤቱ በሚያወጣቸው መመሪያና ስታንዳርድ መሠረት የሚከናወኑ መሆኑ እና በዚሁ መሠረት ክትትል እና ቁጥጥር የሚደረግ መሆኑን ማጣራት፣ | 2.1 ከህክምና ተቋማት የሚወጡ ቆሻሻዎች በዓይነት እና ከሌሎች ቆሻሻዎች ተለይተው ሊቀመጡ ይገባል፡፡ |
| | | 2.2 ህክምና ቆሻሻ ማከማቻዎች/Containers/ በአለም አቀፍ ደረጃ በተቀመጡ መለያዎች/color coding/ መሰረት ሊለዩ ይገባል፡፡ |
| | | 2.3 ስለታማ ያልሆኑ ነገር ግን በሰው ጤና ላይ ጉዳትን የሚያደርሱ የህክምና ቆሻሻዎች ማከማቻዎች ላይ አለም አቀፍ ምልክት (interanational biohazard symbol) () ሊኖር ይገባል፡፡ |
| | | 2.4 ለቆሻሻ ማስወገጃ የሚያገለግሉ የቆሻሻ ማጠራቀሚያዎች በተወሰነ ጊዜ ሊታደሱ ይገባል፡፡ |
| | | 2.5 በልዩ ልዩ የህክምና ክፍሎች ሆነ በቆሻሻ ማጠራቀሚያ አካባቢ የሚያገለግሉ የቆሻሻ ማጠራቀሚያዎች ሊሟሉ ይገባል፡፡ |
| | | 2.6 ከጤና ተቋማት የሚወጡ ቆሻሻዎችን ማጠራቀሚያ የጤና አገልግሎት ከሚሰጥበት 30 ሜ ሊርቅ ይገባል፡፡ |
| | | 2.7 ከህክምና ተቋማት የሚወጡ ቆሻሻዎች በጤና ባለሞያ ተለይቶ ሊወገድ ይገባል፡፡ |
| | | 2.8 በሆስፒታሎችና በክሊኒኮች በቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ላይ ለሚሰሩ ሰራተኞች የስራ ኃላፊነትና ተግባራት በጽሑፍ ተዘጋጅቶ ሊደርሳቸው ይገባል፡፡ |
| | | 2.9 ከህክምና ተቋም የሚወጡ ቆሻሻዎች በየቀኑ ሊሰበሰቡ ይገባል፡፡ |

| | | |
|---|---|---|
| | | 2.10 ከጤና ተቋማት የሚወጡ ቆሻሻዎች በተዘጋጀላቸው የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ውስጥ ያለመዝረክረክ መቀመጥ /መወገድ/ አለባቸው፡፡ |
| | | 2.11ከሰውነት ክፍል የሚወጡ ቆሻሻዎች በፕላስቲክ ወይም ጋልቫናይዝድ ኮንቴነር መከማቸት አለባቸው፡፡ |
| | | 2.12 አደገኛ የሆኑና የተበከሉ ቆሻሻዎች ሳይታከሙ በምንም አይነት መንገድ መወገድ የለባቸውም፡፡ |
| | | 2.13 የህክምና ቆሻሻ ማስወገድ ስራ ላይ የተሰማሩ ሰራተኞች የመከላከያ አልባሳት ሊሟሉላቸው ይገባል፡፡ |
| | | 2.14 የህክምና ቆሻሻ በሚጓጓዝበት ወቅት የህክምና ቆሻሻ አወጋገድ መመሪያን ተከትሎ ሊሆን ይገባል፡፡ |
| | | 2.15 ከጤና ተቋማት የሚወጡና በሽታን ሊያስተላልፍ የሚችሉ(infectious waste) የሚባሉት ቆሻሻዎች በሚጓጓዙበት ወቅት ተዘግተው ሊሆን ይገባል፡፡ |
| | | 2.16 ከተለያዩ ተቋማት የሚወጡ ክልል ተሻጋሪ የደረቅ እና ፍሳሽ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ በህዝብ ጤና ጉዳት የማያስከትል መሆኑን ሊቆጣጠር እና ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ |

## አባሪ 2

## <u>በናሙና ተመርጠው የታዩ የግል የጤና ተቋማት</u>

በአዲስ አበባ ፡-

1. ቅዱስ ገብርኤል ሆስፒታል
2. ቤቴል አጠቃላይ ሆስፒታል
3. ቤተዛታ ሆስፒታል
4. ኪዩር ሆስፒታል
5. ድንበሯ ሆስፒታል
6. ዮርዳኖስ ሆስፒታል
7. ሀያት ሆስፒታል
8. ላንድማርክ ሆስፒታል
9. ተክለሀይማኖት ሆስፒታል
10. ዩኒቨርሳል ከፍተኛ ክሊኒክ
11. ሰናይ ከፍተኛ ክሊኒክ
12. ብሉናይል ከፍተኛ ክሊኒክ
13. ቅድስት ማርያም ከፍተኛ ክሊኒክ
14. ቪዠን ከፍተኛ ክሊኒክ
15. የኗላሸት ከፍተኛ ክሊኒክ

በደቡብ ክልል፡-

1. አሴር ሆስፒታል
2. ቤተ አብርሃም ሆስፒታል
3. ክብሩ ሆስፒታል
4. ክርስቲያን ሆስፒታል
5. ሀዋሳ ከፍተኛ የህፃናት ክሊኒክ
6. ገሊላ ከፍተኛ ክሊኒክ
7. ሀይቅ ዳርፖሊ ክሊኒክ
8. ዋቆ ጥቁር ውሃ ከፍተኛ ክሊኒክ
9. ሉቃስ ክሊኒክ
10. እንያት ክሊኒክ
11. ቤተሳይዳ አንድነት ክሊኒክ
12. ቤተልሔም ክሊኒክ

በኦሮሚያ ክልል፡-

1. መድኃኒዓለም አጠቃላይ ሆስፒታል
2. አኪልሲያ አጠቃላይ ሆስፒታል
3. አዳማ አጠቃላይ ሆስፒታል
4. ምስክር ከፍተኛ ክሊኒክ
5. መድህን ከፍተኛ ክሊኒክ
6. የቤተልሔም ከፍተኛ ክሊኒክ
7. ዶ/ር ተክለጮለሞ ከፍተኛ ክሊኒክ
8. ሉቃስ ከፍተኛ ክሊኒክ
9. አሰላ ከፍተኛ ክሊኒክ
10. መናኸሪያ ከፍተኛ ክሊኒክ
11. ዶ/ር ከድር ሞንጀ ዋቆ ከፍተኛ ክሊኒክ
12. ዶ/ር አሸብር ሱራፌል እስፔሻል ክሊኒክ
13. ዶ/ር አሰፋ ለማ ከፍተኛ ክሊኒክ
14. ዶ/ር ፍቃዱ ከፍተኛ ክሊኒክ
15. ቦሌ መካከለኛ ክሊኒክ